# ጥበቡ

(የምድረበዳው እረኛ)

የዶክተር ጥበቡ ኃይለሥላሴ የሕይወትና የአገልግሎት ታሪክ

*From the Library of*

***ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃንስ***

***FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES***

በሊሻን አጎናፍር

ኤዲተር፡- ወንድዬ ዓሊ

ጥበቡ
የምድረ በዳው አረኛ
በሊሻን አንግፍር © 2013
Biography of Tibebu Haileselassie
Denver,Colorado
August, 2013
*1st edition was published simultaneously, in the United States of America and Ethiopia in Agust, 2013 by:-*
Bang Printing
28210 N. Avenue Stanford,
Valencia, CA 91355
በኢትዮጵያ የመጀመሪያው እትም፡- ነሐሴ 2005
ሁለተኛ እትም ፡- ህዳር 2006
በርኅቦት አተሚዎች ኃ. የተ. የግ. ማህበር፣
የመ. ሣ. ቁ. 100832፣
አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ

ሦስተኛው እትም፡- የካቲት 2006
የመስቀል ምንጭ ማተሚያ
ስልክ 251-11-46724435
ሞባይል 251-9-11513832
ኢሜል፡- ethiopia@sourcelight.org
የመ. ሣ. ቁ. 100595

አራተኛ እትም ሚያዝያ 2006
በርኅቦት አታሚዎች ኃ.የተ.የግ.ማህበር
ስልክ 0114 169027
የመ.ሣ.ቁ.100832

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
Copyright © 2013 በሊሻን አንግፍር

የሽፋን ስዕል፡- አብርሃም ወልደ ገብርኤል
ገጽ ውበት፡- ሳሙኤል ገብረ ሚካኤል (አሜሪካ)፣ ካሌብ በለጠ እና ፀጋው ተሰፋ (ኢትዮጵያ)

ALL RIGHTS RESERVED. This book contains material protected under International and Federal Copyright Laws and Treaties. Any unauthorized reprint or use of this material is prohibited. No part of this book may be reproduced or transmitted in any form or by any means, electronic or mechanical, including photocopying, recording, or by any information storage and retrieval system without express written permission from the author / publisher.

**መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው::** ይህን መጽሐፍ ወይም ማንኛውንም የመጽሐፉን ክፍል ለማባዛት ለመገልበጥ ለመቅረጽ ወይም በሌላ መጽሐፍ በሰፋት ለመጥቀስ አይቻልም ሆኖም ግን ለጥናት ፤ለማስተማርያንት ለመሳሰሉት ዓላማዎች ማንኛውም ግለሰብ፤ ቡድን ወይም ድርጅት ከዚህ መጽሐፍ ለመጥቀስ ቢፈልግ የመጽሐፉን ስም የደራሲውን ስምና መጽሐፉ የታተመበትን ዓ ም የመጥቀስ ግዴታ አለበት።

የደራሲዋ አድራሻ፡-
የመ. ሣ. ቁ. 19005
አዲስ አበባ
ስልክ፡- 09-1291-4460
Email:- lish4jc2000@gmail.com
www.tibebu.org

Printed in Addis Ababa, Ethiopia

መታሰቢያነቱ፥-

ለውድ ባለቤቴ ለጥበቡ ኃይለሥላሴ፣

በእርሱም ሆኖ ታሪክ ለሠራው ለታላቁ እግዚአብሔር፤

ለምወዳቸው ልጆቼና ለወጣቱ ትውልድ፤

ደግሞም

በስደት በመከራና በብዙ መሥዋዕትነት

በዱር በገደሉ ክርስቶስን በመስበክ ትውልዳችንን ለማትረፍ

ለተዋደቁልን

የወንጌል አርበኞች፣

ለቤተክርስቲያንና ለእግዚአብሔር ሕዝብ ይሁንልኝ።

# ምስጋና

ሁሉን ችለህ ሁሉን ያስቻልከኝ **አምላኬ ልዑል** እግዚአብሔር ሆይ! ከአንተ ፍጹም ረድኤት የተነሣ በባሪያህ ሕይወት የተገለጠውን- **እጅግ ጠሊት**፣ ረቂቅና ድንቅ የሆነውን አሠራርህን ለመተረክ አበቃኸኝ። ግሩምነትህን ለመተረክ **ራሴን በሰጠሁት** መጠንም ሃዘኔን አስረሳኸኝ። እኔንም በተራዬ እስከምትጠራኝ የተለየሁትንም **ባሪያህን በመንግሥት**ህ እስካየው ድረስ መቆያ ሰጠኸኝ፤ መጽናትና ብርታት ሆንከኝ። በኩር **ምስጋናዬን እነሆ**! ከዘላለም እስከ ዘላለም ተመስገን!

የሰላሳ ሰባት ዓመት **የትዳር ጓደኛዬ ዋበቡ** ኃይለሥላሴ፣ ልጆቻችንም እምነት፣ ረቂቅና ትደነቅ፡- የዘላለሙን አምላክ **መልካምነት ሁልጊዜ** እንዳወራ ለእኔ የተሰጣችሁኝ ዕንቁዎቼ ናችሁ። በእናንተ የተገለጠችው **መልካሟ የእግዚአብሔር** እጅ የዚህ መጽሐፍ ባሪያና ግድግዳ ሆና ተገኘችልኝ።

ምስጋናዬ ለእግዚአብሔር ሕዝብ እጅግ ብዙ - ብዙ ነው። እግዚአብሔር በዚህ ቤተሰብ ሠርቶ ማሳየት ለሚፈልገው **ክቡር ዐላማው** ተረባረባችሁ፤ በጸሎት በእንባ፣ በተግባር በተገለጠው ፍቅራችሁ አማካኝነት በዙሪያችን **ቆማችሁ**። ይህም መስጠታችሁ መጽሐፉ የአንድ ቤተሰብ ታሪክ ብቻ ሳይሆን የእናንተም **ጭምር** እንዲሆን አደረገው። በታሪካችን ውስጥ ድርና ማግ ሆናችሁ ውበት ሰጣችሁን። በእውነት እግዚአብሔር ያከብርልኝ!

ምሕረት (ሜርሲ) ሙሉዋን ቀም ነገረኛ የሆነችና ወጣት የጋዜጠኝነት ሙያ ምሩቅ ነች። አዲሱ ትውልድ የአጻጻፍ ዘይቤዬንና ቋንቋዬን ይልቁንም መልእክቴን ይረዳልኝ እንደሁ እርግጠኛ ባልነበርኩበት ወቅት በኢትዮጵያ ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ ጽሑፎቼን ያሳየሁት ለእርሷ ነበር። ረቂቁን አንብባና ለትውልድ አቻዎቿም አስነብባ፣ ኖኅ እንደላከት ርግብ መልካም ዜና ያመጣችልኝ ያበረታታችኝ ሜርሲ ናት፡ "የኔው የድሮ አማርኛ ለዛሬዎቹ ወጣቶች አስተርጓሚ ያስፈለገው ይሆንን?" የሚለው ስጋቴ በእሷ ተሻረልኝ። ጌታ አብዝቶ ይባርክሽ! የኔ ልጅ፣ የኔ ቅመም።

ከወንድም ንጉሤ ቡልቻ ውስጥ በሚፈልቀው የእግዚአብሔር ቃልና የመልእክቱ ጉልበት እድል ባገኘሁባቸው ጥቂት ጊዜያት ተጠቅሜያለሁ። ቤተሰቡን የማግኘትና የማወቅ ዕድል የገጠመኝ ግን በዚህ መጽሐፍ ምክንያት ነበር።

ባለቤቱ ማክዳ ግምገማዋ መንፈሳዊ መልእክቱ ላይ ያተኮረ ነበር፤ እይታዋ እንዴት ጠቀመኝ መሰላችሁ! ልጃቸው ኤፍራታ ትውልዷን ወክላ ጽሑፌን ትገመግምልኝ ብዬ ተመኝኋት፤ ተንዛዝቼ እንዳለሰለቻት ግን ፍርሃት ነበረብኝ። በውስጥም በውጭም ውብና ብሩህ አእምሮ ያላት እሷ ከምኞቴ ውጭ አድርጋኛለች፤ የሰጠቻቸውም አስተያየቶች መሬት የሚወድቁ አልነበሩም።

ወንድም ንጉሤ በሕይወትህ የተቀበረው የቃሉ ዕንቁ አሁንም ለብዙዎች እንዲያበራ ይህን የተባረከ ቤተሰብ ስለሰጠህ ጌታን አከብሬአለሁ። ስፋትና ጥልቀት ያለው የቋንቋ ችሎታህ አስገርሞኛል። ከረጃጅም ዐረፍተ ነገሮቼ ጋር ደህና አድርገህ አቆራርጠኸኛል! ስለሰጠኸኝ ገንቢ አስተያየትና በጽሑፉ ላይ ስላደረግኸው አስፈላጊ እርማት ሁሉ ጌታ ይባርክልኝ።

ኤዲቶርያል ኮሚቴ እንዲሆኑልኝ የጋበዝኳቸው፣ አቶ ንጉሤ ቡልቻና ባለቤቱ ወ/ሮ ማክዳ እንዲሁም ልጃቸው ኤፍራታ፣ እህቴ ወ/ሮ ጀሚላ ኢብራሂምና ወይዘሪት ምሕረት አስግድ ናቸው። እህቴ ጀሚላ በሰነጽሁፍና በቋንቋ ችሎታዋ ተደንቄያለሁ። ባደረገቻቸው እርማቶችና በሰጠችኝ ገንቢ አስተያየቶቿ ብዙ ጉልበትና ድፍረት ሆናኛለች። ጽሑፌን እንዲገመግሙልኝ ከእነዚህ ወገኖቼ ጋር ለጥቂት ቀናት ከአዲስ አበባ ወጣ አልን። የመጽሐፉ አጠቃላይ ይዘት መልክ እንዲኖረው፣ ቋንቋው እንዲታረቅ የረዱኝና የመከሩኝ እነሱ ናቸው። ለሰዐታት አብረን ተቀመጥን። የማልረሳቸው የጸሎት ወቅቶች ተከፈቱልን፤ አንዳንዴም በባለታሪኩ በጌታ ፊት አብረን አለቀስን። ልባዊ ምስጋናዬንና አክብሮቴን አቀርባለሁ። ተባረኩልኝ ወገኖቼ!

ሌላ ኮሚቴ ደግሞ ነበረኝ፣ ከሶማሌ ምርኮ ተመላሾች የተውጣጣ። እነርሱ ከባለቤቴ ጋር አሥራ አንድ ዓመት ሙሉ አብረውት ስለነበሩ ታሪኩ ታሪካቸው ነው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ

የተረክሁትን ትረካ የፈተሹልኝ እነሱ ናቸው።

እነዚህ ወገኖቼ ሰበሊ ከበደች ተክለአብ ከአሜሪካ፣ ሲስተር በላይነሽ ቦጋለ፣ አቶ ጥላሁን አትሬቦና አቶ ተስፋዬ በለጠ ደግሞ ከኢትዮጵያ ናቸው። እንደዚያኛው ኮሚቴ አብረን ለቀናት ባንቀመጥም ለሰዐታት ተቀምጠናል። ከሲስተር በላይነሽ ጋራ አብረን ሌሊቶች አሳልፈናል፤ የረሳሁት፣ ያጋነንኩት ወይንም ያልሆነ ታሪክ የዘገብኩት ካለ መረመሩልኝ። ብዙ ደገፉኝ፣ ብዙም አበረታቱኝ። የሌሉኝንም አንዳንድ የታሪክ ክፍሎች አበረከቱልኝ። እግዚአብሔር አምላክ ያከብርልኝ ይባርክልኝም! እወዳችኋለሁ።

አርዓያ ለገሠ፤ ኮምፒዩተር ውስጥ መግባት ያለባቸውን ታሪካዊ ዶክዩመንቶች ፎቶዎች ጊዜ ወስዶ በሚገባ ያዘጋጀልኝ እሱ ነው። ቢሮዬ ወስጥ ያሉትን ኮምፒዩተር ነክ ነገሮች በሙሉ ያያዘልኝ በቴክኖሎጂው የተካነ ወጣት ነው።

ከአገሬ ይዣት ወደ አሜሪካ ያመጣኋት ላፕቶፔ የዚህ መጽሐፍ ሥራ ሳያበቃ እሷ አበቃላት! አዲስ ላፕቶፕና አዲስ የአማርኛ ሶፍት ዌር አስፈለገኝ። አዲስ አበባ ቆጭ ብሎ አሜሪካ ኮምፒዩተሬ ውስጥ ገባ፤ እኔ የማየውን እሱም እያየ ላፕቶፔ ውስጥ ጉድ ጉድ ሲል "ምትሃት ነው ወይንስ ምን?" አልኩኝ! ሰው እንዲህ ባለ በረቀቀ ዕውቀቱ ስንትና ስንት ሺ ኪሎሜትር ርቀት ላይ ለነበርኩት ችግረኛ መድረስ ከቻለ፣ ሁሉ የሚቻለው አምላኬማ ምንኛ!? ሳይንቲፊክ እርዳታህ በጌታ ላይ ያለኝን የእምነት ጉልበት ጨምሮልኛል! አርዓያ ተባረክ!

ወንድሞቼ ገብሩና እንግዳወርቅ አገናፍር የረዳችሁኝ ብዙ ነው፤ ወንድሜ ገብሩ የልጅነትና የቤተሰብ ታሪካችንን በሚመለከት፣ መጽሐፉንም በማንበብ፣ አስተያየት በመስጠትና በማረም አገዝከኝ። አዲስ አበባ ሳለሁ ሌትና ቀን ለመጻፍ ባደረግሁት ትግል፣ ምግብ በሰዐቱ እንድበላ፣ ዕንቅልፍም እንድተኛ ያስገደድከኝ በጸሎትህና በምክርህ የደገፍከኝ ጠቀመኝ። ተባረክ! ወንድሜ እንግዳ አሜሪካ ከመጣሁ በኋላ ታሪኩን አብረን በመናበብ፣ የገደሉኝን ታሪካዊ ፎቶዎች ኮምፒዩተር ላይ በመጫን አብረን ስላሳለፍናቸው ሌሊቶች ተባረክ! ትዕግስት ወረደ! የበፊት ጽሁፎቼ አሁን ከሠራሁበት የአማርኛ ሶፍትዌር ጋር እንዲስማማ ስለረዳሽኝ ተባረኪ!

የናይሮቢው የሕብረት ቤተክርስቲያን አገልጋይ ወንድም መሠረት! በቤተክርስቲያኒቱ አመሠራረት ላይ ሳልጠቅስ የዘነጋሁትን ለማመሳከር የሚጠቅመኝን ዶክዩመንት ሳከልኝ ተባረክ የኔ ወንድም!

የዚህን መጽሐፍ ገጸ-ውበት ለመሥራት በአሜሪካ አታሚዎች ስታንዳርድ ለማዘጋጀት የገጠመኝን የመጨረሻ ፈተና የተወጣሁት በሳሙኤል ገብረሚካኤል ነበር፤ ለሁለተኛው እትም ቅርጽና ውበት ደግሞ ካሌብ በለጠ እና ፀጋው ተስፋ! ሥራቸውን ጠንቅቀው የሚያውቁ ስለሆኑ የረዱኝ እጅግ ብዙ ነው። በቅንነትና በተሰጠ ልብ አብረውኝ ቆሙ፤ ተባረኩ ወንድሞቼ።

ለዚህ መጽሐፍ ሽፋን በብዙ ፍቅርና ማስጠት ታሪኩን የሚወክል ስዕል ለመሥራት ብዙ ያሰብክልኝና የለፋህልኝ ሰዐሊው አብርሃም ወልደ ገብርኤል! ተባረክ! የልቤ እስኪደርስ ሳይታክትህ ስለሠራህልኝ ውብ ሥራ አመሰግናለሁ!

ወንድሜ አቶ ወንድዬ ዓሊ፤ መጽሐፉ ባሰብኩት ጊዜ ለሕትመት ላይደርስ የገጠመኝን የአርታኢ ችግር ይዤ ባለቀ ሰዓት ስሄድበት ተቀበለኝ። ጌታ ይባርክህ ወንድሜ። "ሥራሽ ምንም አይጎድለውም። ተወልዷል። የእኔ ድርሻ እንደ አዋላጅ ነርስ፡- እትብቱን የመቁረጥና የመቋጠር፣ የማጸዳዳት . . . አድርገሽ ቁጠሪው፤" ስትል አጽናናኸኝ አረጋጋኸኝ።

የተናገርከውን ቃል ተግባራዊ ለማድረግ ከለብህ የሥራ ጫና ጋር ይሄን "ድንገቴ" ባጭር ጊዜ ውስጥ ሌትና ቀን ብለህ ልታገላግለኝ የምትችለውን ሁሉ አደረግህልኝ። አቶ ወንድዬ ያልከውን አድርገሃል፤ አንባቢዎቼ ያለችግር ይህን ታሪክ አንብበው ባለታሪኩን ጌታ እንዲያዩት እውነትም አጸዳዳህልኝ። ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው።

ሊሻን አገናፍር

# በምስጋና ላይ ምስጋና

<<ጥበቡ - የምድረበዳው እረኛ>> ለመጀመሪያ ጊዜ ለአንባቢዎች የቀረበዉ ነሐሴ 25 ቀን 2005 ዓ.ም ነበር። በሰባት ወራት ውስጥ ሁለት ጊዜ ታትሞ ----- ሁሉም ቅጅዎች ተሰራጩ። ያልጠበቅኹት ስኬት ነበር። አሁን ደግሞ፣ እነሆ ለሦስተኛ ጊዜ ታተመ።

መጽሐፉን ለማዘጋጀት ስነሳ ሁለንተናን በሚመረምር በእግዚአብሔር ፊት ትሁት ልቡና ቅን መሻት፣ በጎ ዓላማ ተላብሼ እንደነበረ አስታውሳለሁ። ጥረቴም በቅዱሳን ብርቱ ጸሎትና ምክር የተከበበ ስለመሆኑ ትዝታዬ ትኩስ ነዉ።

አንድ ነገር አውቃለሁ። መንፈስ ቅዱስ በልቤ እንዳሳደረው አደራ መጠን፡- ያየሁትን፣ የሰማሁትንና የዳሰስኩትን ወረቀት ላይ አስፍሬ ኃላፊነቴን ከመወጣት ያለፈ ሙከራዬ ይህን ያህል ተነባቢ፣ ተፈላጊና ጠቃሚ ይሆናል ብዬ አላሰብኩም ነበር። በእውን ሳየዉ ግን ነፍሴ መደነቅን ተደነቀች። ይህችን የምስጋና ማስታወሻ ለሦስተኛው ዙር ሕትመት መሸኛ አድርጌ እንዳቀርብ ምክንያት ሆነኝ።

አስቀድሜ፡- የመልካም ምንጭ ሁሉ ባለቤት የሆነውን ጌታ አምላኬን አመሰግናለሁ። ለሙከራዬ ውበትና መዓዛ የጨመረለት እሱ ነውና። ቃሌን እንደ ቃሉ አጽንቶ፣ ለጥበቡ ሐውልት ያቆመለት እሱ እግዚአብሔር ነውና። ጌታ ሆይ! አጥንቴም ጅማቴም ያመሰግኑሃል።

ሁለተኛም፡- የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንን አመሰግናለሁ። መጽሐፉን እንደ ስምዖን (ሉቃ2፡25-32) ተቀብላ አቀፈችልኝ። አቅፋም መረቀችልኝ። መድረከም ከፈተችልኝ።

ሦስተኛም፡- እስፖንጅ ፈሳሽን እንደሚመጥ፣ ባለፉት ሁለት ዙሮች የታተሙትን ቅጅዎች በየመደብሩ ከዐይን እስኪታጡ ድረስ ለመግዛት የተረባረበዉን የእግዚአብሔርን ሕዝብ አመሰግናለሁ። በተለይም አንብበው፣ ተንትነው፣ አስተንትነው ... ለገዛ ሕይወታቸው፣ ለቤተሰባቸውና ለቤተክርስቲያንም ጥቅም ያደረጉት ደግሞ እጥፍ ድርብ ምስጋና ይገባቸዋል።

መጽሐፉ እንዲህ ለቤተክርስቲያንና ለልጆቿ ጥቅም ሲውልና የውዴ የጥበቡ አገልግሎት ከሞት ወዲያ ማዶ ሲቀጥል ምስክር ያደረገኝ ጌታ እግዚአብሔር ክብር ይሁንለት።

ብሩክ ሁኑ!
ከፍጹም አክብሮትና ትህትና ጋር
ሊሻን አንዳፍር

# መቅድም

ዐይኑ ጥልቅ ርኅራኄን ይገልጣል፤ በልቡ ውስጥ ያለው ርጋታ በገጹ ላይ ይነበባል። በለዘብታ ፈገግ ያሉት ከናፍሩ ደግነቱን ያውጃሉ። ሰውየው እንዳች አባታዊ፤ ወንድማዊ ካኅናዊ ወዘና አለው። በላሎኑ የቀኝ ግድግዳ ላይ የተሰቀለው ይህ ፎቶግራፍ በአንድ ዐይን ውርወራ ብቻ የዚህን ሰው ማንነት ከሰተው። ደስ የሚል ሰው ነው።

እኔ እንግዲህ ገና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሆኜ ስለ ሦስት ብርቱ ክርስቲያን ሐኪሞች ሰሰማ ቆየሁ። አንዱ ዶክተር ጥበቡ ኃይለሥላሴ ነበር፤ ሌሎቹ ዶክተር ብርሃኑና ዶክተር ሚልክያስ ነበሩ። አሁን ሦስቱም በተባረከው ጌታ እቅፍ ውስጥ ናቸው።

ከጋሽ ጥበቡ ጋር ለማውራት ዕድል ያገኘሁት ግን አሁን በቅርቡ ከሠላሳ አምስት ዓመት ግድም በኋላ በጠና ታሞ ዴንቨር ከተማ በቤት ውስጥ ነው (ለአሥር ደቂቆች ያህል አውርተን ይሆን?)። ንግግሩ ሁሉ የፅኑ እምነት መግለጫ ነበር፤ እኔ በኀዘኔታ በለሆሳስ ላናግረው ስሞክር፣ እርሱ በርግጠኝነት በነቃ መንፈስ እኔኑ መልሶ በሚያበረታ የፍቅርና የተስፋ ድምፅ ይመልስልኝ ነበር፤ አቤት ጽናት! አቤት ደልዳላ እምነት! ·

ይህ ሰው ከሚወደው ቤተሰቡ ጋር እንዲሁም በትልቅ የኃላፊነት ስሜት ከሚያገለግላቸው ልዩ ልዩ ሕዘቦች ጋር በተለይም ከጌታውና ከአምላኩ ጋር በታማኝነት የኖረውን አስደናቂ ሕይወት ጉዞ ደግሞ ሳነብና ስሰማ፣ ወይ ግሩም እያልሁ የደስታ የምስጋናና የርካታ ድባብ ነገሠብኝ። ክብር ለመድኃኒዓለም ይሁን!

በእነዚህ ገጾች ውስጥ የጋሽ ጥበቡ ታሪክ ያለ ቋጥኝ፣ ያለ እንቅፋት እንደሚተምም ጅረት በርጋታ ይፈስሳል። ጸሐፊዋ ሊሻን የሰከነ፣ የተገራ ብዕር አላት። በልቧ ማኀደር ስንት የሚንተገተግ የስሜት እሳት እያለ ጽሑፉ ደርዝ ይዞ መሔዱ በእግዚአብሔር ጸጋ ታሽቶ የለዘበ ሰብዕና ውጤት ይመስለኛል። ይሁን እንጂ በየፈቀቅታው የፅኑ ፍቅር፤ የናፍቆት፤ የአድናቆት የተስፋ፤ የጉጉት ዜማዋ አልተደበቀም።

የጋሽ ጥበቡ ሕይወት እግዚአብሔር ከአንድ ራሱን ሳይሰስት ካቀረበ ሰው ጋር ሊሠራ የሚችለውን ውብ ሥራ የሚመሰክር ነው። በትጋት የተኮተኮተ የእግዜር-ጋር ባልንጀርነት ሕይወትን ፍሬያማም ድላዊም እንደሚያደርግ በይፋ ያሳያል።

የሰው ልጅን የባህል፤ የዘር፣ የሃይማኖት፤ የቀለም ልብሱን ዘልቆ ጥሬ ማንነቱን ማክበርና መውደድ እንዴት ታላቅ የለውጥ ጉልበት እንደሆነ በዚህ ሰው ሕይወት አየን። ይህ መጽሐፍ እንድም እያደር እየፈካ እየደመቀ የሚሄድ ጽኑ የቤተሰብ ፍቅር ግብዣ ነው። በውሉ፣ ወጀብ ያላናጋው፤ ዳሩ ግን በታላቅ የእምነት ጽናትና የፍቅር ኃይል እየተጋመደ ከትናንት ዛሬ እየበረታ የቆመ የሚያስቀና ቤተሰብ ነው።

ሐኪሙ ጥበቡ የፍቅር አምባሳደር ሆኖ፣ የክርስቶስ ወንጌል ዐርበኛ ሆኖ፣ የውድ ቤተሰቡም መሪ ሆኖ ሁላችንን የሚያረካ ሕይወት ኖረ። እኛ የቀረን ሰዎች ልንኖርለት የሚገባን ከፍ ያለ የሕይወት ዓላማ ምን እንደሆነ እንድንፈትሽ የሚሞግት ሕይወት ኖረ። ሐዋርያው ጳውሎስ ጥንፍፍ አድርጎ የኑሮ ዓላማችንን ጽፎልናል። "አንዱ ስለሁሉ ሞተ፤ እንግዲያስ ሁሉ ሞቱ፤ በሕይወትም ያሉት ስለእነርሱ ለሞተውና ለተነሣው እንጂ ወደፊት ለራሳቸው እንዳይኖሩ ስለሁሉ ሞተ" 2ቆሮ 5፥14-15።

የመኖር ዓላማችን፣ የሞታችንን ዓይነት ይወስነዋል። የሞት ዓይነት ሲባል የምንሞትበት ዕድሜና የወዲያው ምክንያቱን ማለቴ አይደለም፤ ትተነው የምንሄደውን ቅድመ ሞት ሕይወት ዋጋ ማለቴ ነው። ያኔ ሞታችን ያስቀናል! "የጻድቁን ሞት እኔ ልሙት፤ ፍጻሜዬም እንደ እርሱ ፍጻሜ ትሁን" ዘኍ 23፥10።

ንጉሤ ቡልቻ   ቃለ እግዚአብሔር እንባብያን



ዶክተር ጥበቡ ኃይለሥላሴ

# ማንደርደሪያ

"ይኸ የብዙ አገሮች ታሪክ ነው፥- የ ኃይለሥላሴዋ እና የመንግሥቱ ኃይለ ማርያምዋ ኢትዮጵያ፥ የዚያድ ባሬዋ እና የመንግሥት የለሽዋ ሶማሊያ፥ የሱዳን፥ . . ። ይኸ የብዙ ድርጅቶች ታሪክ ነው የ UNICEF, UNHCR, ICRC, LIVING BIBLES INTERNATIONAL, ሕያው ተስፋ ሬድዮ፥ ብርሃን መጸሔት፥ WORLD VISION INTERNATIONAL..። ደግሞም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም ታሪክ ነው። ለምክንያትነት የተመረጠው ቤተሰብ በተዘዋወረበት ሁሉ - በኢትዮጵያ፥ በሶማሊያ፥ በኬንያ፥ በሱዳን፥ በሌሶቶ፥ በእስራኤል፥ በቶሮንቶ፥ በዴንቨር፥ . . .። ይኸ የብዙ ሰዎችም ታሪክ ነው - የወንዶችና ሴቶች፥ ሕፃናትና ታዳጊዎች፥ ወጣቶች እና ጎልማሶች፥ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች፥ ወዘተርፈ። በዚህ ታሪክ ዙሪያ እስከሁን ሁለት መጻሕፍት ተጽፈዋል - አንዱ በአማርኛ፥ ሌላው በስዊድንኛ፤ ይኸ ሦስተኛው መሆኑ ነው፤ የመጨረሻው ግን አይሆንም።

ለታሪኩ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ሲጀምር፥ እግዚአብሔር አንድ ቤተሰብ መሠረተ፤ መስከረም 10 ቀን 1968 ዓ.ም. ዶክተር ጥበቡ ኃይለሥላሴ እና ወይዘሪት ሊሻን አንገፍር በቃል ኪዳን ሲጋቡ። ቤተሰቡንም በቅዱስ ቃሉ፥ በጾምና በጸሎት፥ እንዲሁም በትንቢት፥ በቅድመ ዝግጅቱ ውስጥ አካተተ። ሐምሌ 17 ቀን 1969 ዓ.ም. የቤተሰቡ ሁለተኛ ልጅ ተወለደች - በናዝሬት። በዚያው ዕለት የሊሻን አያት ሞቱ - እዚያው ቤት። በዚያው ዕለት ዶክተር ጥበቡ ኃይለሥላሴ ከብዙ ሺህ ኢትዮጵያውያን ጋር ተማረከ፤ በሶማሊያ መንግሥት ጦር - በሕክምና ከሚያገለግልባት ከቀብሪደሃር። የልጃቸው ስም "ረቂቅ ጥበቡ" ተባለ። የታሪኩ የመጀመሪያ ምዕራፍም ለአሥራ አንድ ዓመታት ተቀጣጠለ፤ ምርኮኞቹ ባሉባት በሶማሊያ፤ ሊሻን እና ልጆቿ - እምነትና ረቂቅ - ባሉባቸውም በኢትዮጵያና በኬንያ።

ዶክተር ጥበቡ ከቤተ ሰቡ ጋር ሲቀላቀል፥ ታሪኩ ወደ ሁለተኛው ምዕራፍ ተሸጋገረ። በተሸጋገረ በስድስተኛ ወሩ ጥበቡ በናይሮቢው የዩኒሴፍ ቢሮ ሥራ ጀመረ። ዓመት ተኩል ያህል እንደ ሠራ፥ ሦስተኛዋ ልጃቸው "ትደነቅ ጥበቡ" ተወለደች። ቤተ ሰቡም በብዙ አገሮች ተዘዋወረ - ሱዳን፥ መንግሥት የለሽዋ ሶማሊያ፥ ሌሶቶ፥ ኢራቅ፥ እስራኤል፥ ካናዳ፥ ኢትዮጵያ፥ ኒውዮርክ። በተዘዋወረበትም ሁሉ እግዚአብሔር ብዙዎችን ተናገረ። የሚማሩ ተማሩ፤ የሚቀየሩም ተቀየሩ፤ ሌሎች ብዙ ታሪኮችም ተጀመሩ፤ ተሠሩ - ባጭሩ። እስከ ኦገስት 30 ቀን 2012 ድረስ። ዕለቱ የትደነቅ ሐያ አንደኛ ዓመት ዕለተ ልደት ነበረ። አሁን ደግሞ በአባቷ ዕለተ ሞትነትም ጭምር ተዘከረ - በዴንቨር፥ ኮሎራዶ።

በእግዚአብሔር ዕቅድ፥ በእምነት እና በጸሎት፥ ግልጽ በሆነም ምሪት፥ ላለፉት ሰላሣ ሰባት ዓመታት የተጓዘው የዚህ ቤተ ሰብ ታሪክ ከማስደነቅ ያልፋል። እንዴ ልታነቡት ከጀመራችሁ ሳትጨርሱት አታርፉም፤ ትስቃላችሁ፤ ታለቅሳላችሁ፤ በእግዚአብሔርም ሁሉን ቻይነት ትደመማላችሁ።"

በቀለ ወልደ ኪዳን
(መጋቢ)

*"...ይህ ታሪክ፣*
*የአንድ ሰው ወይንም የአንድ ቤተሰብ ታሪክ ብቻ አይደለም!*
*የእግዚአብሔር ሕዝብና*
*የዓለም አቀፉ የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተክርስቲያንም*
*ታሪክ ጥምር እንጂ..."*

# ማውጫ


ክፍል 1 ጥበቡ ............. 19

ክፍል 2 የጥበቡ ጥበብ ........67

ክፍል 3 የምድረበዳው እረኛ .....155

ክፍል 4 የጥበቡ ምሪት ........257

ክፍል 5 የጥበቡ ሌጋሲ ........353

# መግቢያ

ባለፈው ጊዜ አንድ ሰው በብዙ ሰዎች ዘንድ የመነጋገሪያ ርእስ ሆኖ ከረመ። በሚያውቁት በማያውቁትም ዘንድ ተሰምቶና ተነግሮ የማይጠገብ እውነተኛ ታሪክ ሠርቶ፣ አምላኩን እግዚአብሔርን አከብሮና አስከብሮ አለፈ። የታሪኩ ባለቤት ራሱ እግዚአብሔር ነው፤ የሚታዘዝለት አግኝቶ ደከማውን ሰው ባለ ታሪክ አደረገው እንጂ።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የሕይወቱ መሪ አድርጎ መከተል ከጀመረበት ከወጣትነት ጊዜው አንሥቶ የሚያውቁት ጓደኞቹ፡- "የእምነት ሰው፣ የፍቅር ሰው፣ የጸሎት ሰው፣ የእግዚአብሔር ሰው፣" ወዘተ... ይሉታል።

በሶማሊያ ምድር አሥራ አንድ ዓመታት በፈጀ የምርኮኝነት ዘመን አብረውት የነበሩ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ደግሞ ስለማንነቱ ሲናገሩ፡- "የክርስትናን ጉልበትና የክርስቶስን ፍቅር በተግባር ያሳየን፣ በእውነት የእግዚአብሔር ሰውነቱን በደማቅ ቀለም የጻፈብን ሕያዋን ምስክሮቹ ነን" ይሉታል።

የሥራ ጓደኞቹ ይመሰክሩለታል፤ እንዲህ ሲሉ፡- "በከፍተኛ ኃላፊነት በተዘዋወረባቸው በተለያዩ አገር ሕዝቦች መካከል ዓለም አቀፍ አስተዋጽኦ ያበረከተ፣ አገሩን ያኮራ፣ ዲፕሎማት፣ ትጉና ምስጉን ሠራተኛ"።

ከአብራኩ የተገኙ ልጆቹ ደግሞ፡- "የጌታ ክርስቶስን ፍቅር ነፀብራቅ በሕይወት ምሳሌነቱ በውስጣችን ቀርጾ ያለፈ፣ በክርስትና ሕይወታችን በዘመናችን ሁሉ የሚያስፈልገንን ትምህርት ያስተማረን፣ በሙሉ የአባትነት ፍቅርና መሥዋዕትነት ያሳደገን አባታችን" ይሉታል።

ይህ ሰው፡- የ37 ዓመታት የትዳር ጓደኛዬ፣ የልጆቼ አባት፣ ከላይ የተባለውን ሁሉ እጥፍ - ድርብ አድርጌ ሳስተጋባለት ውዬ ባድር ደስ፣ የሚለኝ፣ እጅግ የማፈቅረውና የማከብረው ባለቤቴ ጥበቡ ኃይለሥላሴ ነው።

የዚህ መጽሐፍ ዋና ዓላማ ታላቁ እግዚአብሔር በአንድ ሰው ሕይወት ብሎም በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ሲገባ ሊሠራ ስለሚችለውና ስለሚያስችለው አስደናቂና መለኮታዊ ታሪክ ለማውሳት ነው። ታሪክ ሠርቶ ሰውን ባለ ታሪክ ስለሚያደርገው ስለ ፈጣሪ ኩሉ ዓለም ለመናገር ነው።

ከአንድ ዓመት ከአራት ወር በፊት አንድ የምንወደው ወንድማችን ከኢትዮጵያ እኛ ወደ ምንኖርበት አሜሪካ መጥቶ ሳለ፣ ቀደም ሲል ባለቤቴ በገጠመው የጤንነት መታወክ ያሳለፍነውን ውጣ ውረድ፣ ጌታ እግዚአብሔርም ያደረገልንን ታላላቅ ምሕረትና ቸርነት ከባለቤቴ ጋራ ሆነን አጫወትነው። ያ ወንድማችንም፡- "ይሄን ታሪክ ለምን በመጽሐፍ አትጽፊውም? ለብዙዎች በረከትና መጽናናት ይሆን ነበር" በማለት የልቡን አሳብ ሰነዘረልኝ። ባለቤቴ ቀበል አደረገና "ይገርምሃል፤ እሷ እኮ መጻፍ ጀምራለች፤ ጊዜ አጥታ ነው እንጂ። አሁን ጌታ ሲፈውሰኝ አንድ ዓመት ሳባቲካል (ዕረፍት) ትወስድና ያኔ ትጨርሰዋለች፤" ሲል መለሰለት።

ወንድማችን በባለቤቴ አነጋገር ልቡ ተነካ፤ ፊጥኖም ተንበርክኮ በጌታ ፊት እንዲህ ሲል ጸለየ። "አሜን ጌታ ሆይ፤ ከወንድሜ እምነት ጋራ እስማማለሁ። አንተ ፈውሰውና እህቴም ይህን መጽሐፍ ላንተ ክብር ትጻፈው"። ባለቤቴ ይህን በተናገረ በአራተኛ ወሩ፣ ሕመምና ስቃይ ወደሌለበት፣ የማይገመስ ሰላም ደስታና ዕረፍት ወደሞላበት፣ ወደ ዘላለም ቤቱ ተሻገረ። የተናገረው "ምሥጢር

አዘል ትንቢት" መሆኑን አላወቅሁም እንጂ፣ እሱ ሄዶ እኔ በምድር ላይ ቀርቼ፣ ይህ ታሪክ ባለቤቴ እንዳለው በአንድ ዓመት ጊዜው ውስጥ ሊደርስ መቻሉን ሳስብ እደነቃለሁ።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የምታነቡት ታሪክ እውነተኛ ታሪክ ነው። ታሪኩ በአንድ አስደናቂ ሰው ብሎም በቤተ ሰቡ ሕይወት የተፈጸመ የቅርብ ጊዜ ታሪክ ነው። እኔና ባለቤቴ ተወልደን ባደግንባት በአገራችንም ሆነ በውጭ አገር በኖርንባቸው ሰፍራዎች፣ በሺዎች በሚቆጠሩ በሚያውቁን ሰዎች መካከል በእርግጥ የተፈጸመ ታሪክ ነው። የመጨረሻ ልጃችን "ትደነቅ ጥበቡ" እርሷ ከመወለዷ በፊት የተፈጸመውን ታሪካችንን ስትሰማ "እውነት ይሄ ሁሉ ነገር በቤተሰባችን በዚህ ምድር ላይ ተፈጽሟልን?" ትለናለች። እሷ ካደገችበትና ከኖረችበት ልዩ ስለሆነና ታሪኩም "እጹብ ድንቅ" ስለሚሆንባት፡- "አሁን እኔ የተወለድኩት እዚህ ቤተሰብ ውስጥ ነው?" ብላም ትገረማለች። እሷን ያስደነቃትን ያህል በቤተሰባችን የሆነውን ለአንዳንድ ጓደኞቿ ስታወራላቸው፣ ከሆነ ፊልም ላይ ስላየነው ልብ ወለድ ታሪክ የተረከንላት እንጂ፣ በእውን የተፈጸመ አይመስላቸውም።

ታሪኩ በከፊል በ1990 (እኤአ) "በርገር ቴዩረሰን" በተሰኘ ስዊድናዊ ደራሲ ለመጀመሪያ ጊዜ በስዊድን ቋንቋ ተጽፏል። በእንግሊዘኛ ተተርጎሞ አልወጣም እንጂ፣ በኖርዊጅያን፣ በፊኒሽ፣ በዴኒሽ እናም በፈረንሳይ የበርገር ቴዩረሰን መጽሐፍ ተተርጉሞ ወጥቷል። የአሥራ አንዱን ዓመት ታሪካችንን በሚመለከት እኔና ባለቤቴ ሦስት ሳምንታት ያህል በየካቲት ወር 1989 (እኤአ) ናይሮቢ ኬንያ ከደራሲው ጋር ታሪካችንን እንዴት እንዳስመዘገብነው አስታውሳለሁ።

በርገር ቴዩረሰን በመጽሐፉ ካስነበባቸው የአሥራ አንዱ ዓመታት ትውስታዎች የማይተናነስ ሌላ መጽሐፍ የመሚወጣው ታሪክ በሕይወታችን አሳልፈናል። ይህ የእኔ ዝግጅት የፊቱንም የኋላውንም አመጣጥና ለመተረክ ይሞክራል።

መጽሐፉ በ1969 ዓ.ም ሶማሊያ ኢትዮጵያን በወረረችበትና በከፈተችው ጦርነት ሳቢያ በኦጋዴን ይኖር የነበረ በብዙ ሺህ የሚቆጠር ነዋሪ ሕዝብ ግፍ የተቀበለበትን፣ የተሰዋበትንና የተከታዮቹን አሥራ አንድ ዓመታት ጎፍናኝ ክስተቶችን በሰፊው ይዳስሳል።

ይህ ምን ማለት ነው? በአጭሩ፡- በተአምር ከእልቂት ተርፎ በአካባቢው በሕይወት የተገኘው ሲቪል ሕዝብ፣ ጦር መሣሪያ ታጥቆ ያልተዋጋው ዜጋ ሁሉ ለሞት እንደሚነዳ በግ በምርኮ ወደ ሶማሊያ የተነዳበት ታሪክ ነው። በከባድ የባርነት ቀንበር ሥር ለአሥራ አንድ ዓመታት በምሥጢር በተያዘ ስቃይና ግፍ፣ ሰማይ ምድሩ ስለተዘጋበት ሕዝብ የሚተርክ አሳዛኝ ታሪክ ነው። ለምርኮ ከተዳረጉት ወገኖቹ መኻል አንዱ የነበረውና የዚያ ሕዝብ የመከራ ፅዋ ተካፋይ የሆነው የባለቤቴ የጥበቡ ኃይለሥላሴ ታሪክ ነው። ደግሞም የሕዝቤና የአገሬ ታሪክ ነው። የለጋ ትዳሬን በር እንኳክቶ ከባለቤቴ ለአሥራ አንድ አስጨናቂ ዓመታት የለየኝ፣ የእኔ ታሪክ ነው። የልጆቼና በተመሳሳይ የሕይወት ነውጥ ያለፋጽ የአገሬ ልጆች ሁሉ ታሪክ ነው።

የሶማሊውም ሆነ የቀሪው ታሪክ ዋና ምንጭ እኛው ነን፤ ሕይወታችን ነው፤ በሕይወታችን የመጡልንም የመጡብንም የመኖር አላባዎች ናቸው። መጀመሪያም ለስዊድናዊው ደራሲ የጽሑፍ ግብዓት ስንል፣ ኋላም ደግሞ እኔው እጽፈው ዘንድ ቀን ስጠብቅለት ለነበረው ለዚህ መጽሐፍ ስንል ከባለቤቴ ጋራ ያሰባሰብናቸው ማስታወሻዎችና ሰነዶች ናቸው። በዓመታቱ መካከል ሊዘሉን የሚችሉትን ክፍሉ ታሪኮች በሚገባ ልተርካቸው ያስቻለኝ ያኔ በትኩሱ ያደረግነው ቅድመ ዝግጅት ነው።

መጽሐፉን በአምስት ዐበይት ክፍሎች አዋቅሬዋለሁ። "ጥበቡ"፣ "የጥበቡ ጥበብ"፣

"የምድረ በዳው እረኛ"፣ "የጥበቡ ምሪት" እና "የጥበቡ ሌጋሲ"።

ታሪኩ የተፈጸመው በውጭ አገርና በአገር ቤት ነው። ስለሆነም የዘመን አቆጣጠሩን ስሌት ላለማጣረስ ስል በውጪው አገር ለተፈጸመው ታሪክ በሙሉ የተጠቀምኩት የአውሮፓውያኑን አቆጣጠር ነው፤ ወራቶቹንም የጻፍኩት በእንግሊዘኛ በሚጠሩበት ስያሜቸው ነው፤ ለምሳሌ፡- ጁላይ 24/1977። በአገራችን ውስጥ ለተፈጸመው ታሪክ ደግሞ የአገራችንን ወራት ስምና ዓ.ም. የሚለውን አጻጻፍ ተጠቅሜአለሁ።

"ለምን ይሄን መጽሐፍ እስከ ዛሬ አዘገየሽው? በተለይ በሶማሊያ የተፈጸመው ታሪክ ብዙ አልቆየም ወይ?" ያሉኝ ብዙዎች ነበሩ። መልሱ "እውነት ነው፤ ዘግይቷል፤ ቆይቷል" ነው። የስዊድኑ ደራሲ ታሪኩን በስካንዲኔቭያን ቋንቋዎች ካተማቸው በኋላ እኔም በአማርኛችን ልጽፈው ካሰብኩ፣ ከጀመርኩም ቆይቻለሁ። በመሐል ግን ብዙ ጊዜ እየቸገረኝ አቋርጫለሁ። ችግሬ ሌላ አልነበረም፤ በታሪኩ ውስጥ ግልጽና አስገራሚ የእግዚአብሔርን ሕልውና ስለማይ ቋንቋ ያጥረኝና አቆማለሁ። "ይሄ በሰው ቋንቋ እንዴት ይተረካል ጌታ ሆይ? ደግሞስ እንደ ማንኛውም ጽሑፍ እንዴት ወጣ ገባ እያልኩ እጽፈዋለሁ? በጾም በጸሎት፣ በፊትህ በስክነ ልብና መንፈስ ካልሆነ ላደርገው አልችልም" ብዬ ብዙ ጊዜ እየጀመርኩ ትቼዋለሁ። ይህ የትልቁ የእግዚአብሔር ታሪክ ስለሆነ አንባቢዎቼም በዚያ መልኩ እንድትረዱልኝ ጸሎቴ ነው።

ሌላው ምክንያት፤ ባለቤቴ ስለ ጌታ ውለታ እንጂ ስለ እርሱ ብዙ እንዲነገር የሚፈልግ ሰው አልነበረምና እርሱ በሌለበት እንዲነገር እግዚአብሔር የቀጠረው ጊዜ አሁን ባለቤቴ ካለፈ በኋላ ስለሆነም እንደሆን በሚገባ ተረድቻለሁ። በሦስተኛ ደረጃ፤ በዚህ ሰውና በቤተ ሰቡ እግዚአብሔር አምላክ ሠርቶ ማሳየት የፈለገውን አድማሱ እየሰፋ የቀጠለውን ታሪክ፣ ወደሚቀጥለው ትውልድ መሸጋገሪያው ምዕራፍ ላይ ሲደርስ እንዲጻፍ እግዚአብሔር ስለወደደ ነው ብዬም አምናለሁ። አራተኛው ምክንያት፤ እግዚአብሔር አምላክ እኔን ሴት ባሪያውን ከደረሰብኝ ጊዜያዊ ሐዘን ይልቅ በቤቴና በሕይወቴ፣ በዚህም ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው ውስጥ ወደ ተደረገው መለኮታዊ ሥራ ዞር እንድል፣ ለትውልድ ተሻጋሪ ታሪክ ብዕሬን እንዳነሣው ስላደረገ ነው ብዬ እስባለሁ።

እነሆ! ሁለት አሥርተ ዓመታት ያህል ወደ ኋላና ወደ ፊት ይዧችሁ የሚጓዘውን ይህን መጽሐፍ ይዤላችሁ የምቀርበው በትሕትና ነው። እስከ ምዕራፉ መጨረሻ በአሳብ አብረን እንደምንጓዝ ተስፋ አደርጋለሁ። ከሁሉም በላይ ይህ ሙከራዬ ለተለየና ለተሻለ የሕይወት ዋጋ መረዳት፣ እንዲሁም ለከበረ ድምዳሜ ያነቃቃችሁ ዘንድ እጸልያለሁ።

መልካም ንባብ!
ሊሻን አገናፍር

\- - - - - - - - - - - - - -

አሜሪካ 2005 ዓ.ም

"የጭንቀት ቀን ሳይመጣ
በጉብዝናህ
ወራት ፈጣሪህን አስብ፤
ደስ አያሰኙም የምትላቸውም
ዓመታት ሳይደርሱ፤...
አፈርም ወደ ነበረበት
ምድር ሳይመለስ፥
ነፍስም ወደ ሰጠው
ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ
ፈጣሪህን አስብ።"

መክ. 12:1፡7

# ክፍል አንድ

# 1

## የሌሊቶች ሌሊት !

ኦገስት 20/2012። የኔ ውድ አሜሪካ ውስጥ ዴንቨር ኮሎራዶ ሆስፒታል ከገባ ዛሬ ልክ አንድ ሳምንት ሆኖታል። ባለፉት አምስት ዓመታት የእምነትና የተስፋ ተጋድሎአችን፣ ጌታ እግዚአብሔር በድንቅ እየረዳን ሆስፒታል በገባባቸው ጊዜያት ሁሉ ተሽሎት በሕይወትና በጥንካሬ ከሆስፒታል እንደወጣባቸው ጊዜያት የአሁኑ አልሆነም እንጂ። ከመሻሻል ይልቅ እያሽቆለቆለ የመጣውን የውዴን ሁኔታ መቀበል አልቻልንም! እኔም ሆንኩ ልጆቻችን ሞት ከጥበቡ ይለየን ዘንድ ፈጽሞ አልተዘጋጀንምና ግራ መጋባታችን ሐኪሞቹንም ግራ አጋባቸው።

ኦገስት 24/2012 ዕለተ አርብ። ከማለዳው እስከ ምሽቱ ነገሮችን ለመቀበል በሕይወቴ ከተቸገርኩባቸው ቀናት መኻል ዋናውና አንዱ ሆኖ ዋለ፤ ለልጆቻችንም እንዲሁ ቀኑ ከፉ ሆነ። ሁለቱ ትልልቅ ልጆቻችን እምነትና ረቂቅ የዋሉት ሆስፒታል ነው። የመጨረሻ ልጃችን ትደነቅ፣ የአራተኛ ዓመት ትምህርቷን ከሁለት ቀን በፊት ስለጀመረች በዚህ ሰዓት ያለችው ሪጅስ ዩኒቨርሲቲ ካምፓስ ነው። ምሽቱ ላይ ግን ትመጣለች። ትልቋ ልጃችን እምነት ከእኔና ከታናሽ እህቴ ከሰንዱ ጋር ተደርባ ሶስተኛ ሆና አብራን አደረች። ውዴ ግን አሁንም በማይነቃበት እንቅልፍ ውስጥ ነው፤ አንዳንድ አልፎ አልፎ ከሚያሰማው ድምጽ በስተቀር። ነርሶች የሚያደረጉለትን እንክብካቤና ተራቸውን እየጠበቁ የሚሰጡትን መድኃኒቶች ለመቀጠል ይገባሉ። ሶስታችን እርስ በእርስ ብዙ አልተነጋገርንም፤ እንባዬ ድቅን ድቅን ስለሚል። እምነትና ሰንዱ እየገፋ ስለመጣው ሁኔታ ልብ ለልብ ከመተዋወቃቸው አልፈው፣ መወያየትም ጀምረዋል። መነጋገር የቸገራቸው ከእኔ ጋር እንደሆነ ገብቶኛል። በየልባችን የቁንቅና እንደቤተሰብ የመጣብንን የዚህን ሁኔታ ፍጻሜ ላለማሰብ በውስጣችን ስንታገል አደርን። ተፈጥሯዊ ሂደቱን ጠብቆ ያ ሌሊት ነጋ።

****

ጌታዬና አምላኬ በምሕረቱና በርህራሄው በሕይወት ዘመኔ የገጠሙኝን ከባባድ ሌሊቶች እንገቶልኛል፤ አስጨናቂ የሕይወት ወቅቶች አሳልፎኛል! ይሄንንም ከፉ ሌሊትና ወቅት ያነጋልኛል፣ ያሳልፈኛል ብዬ ከማመን፣ መድከም አልፈለግሁም! የዛሬ አምስት ዓመት ገጥሞኝ ወደነበረው "የሌሊቶች ሌሊት" ወዳልኩት፣ በአምላኬ ጉልበት ግን እዚህ ወደ ደረስኩበት የሕይወቴ ወቅት

በሃሳቤ ነጎድኩ። ፈቃዳችሁ ቢሆን እስቲ ያን ሌሊቴን እናንተንም ላስጎብኛችሁ፤ መልካም! አብረን በአሳብ እንጓዝ።

****

ኦገስት 19 ቀን 2007። እኩለ ሌሊት አልፏል፤ እሁድ ለሰኞ አጥቢያ። ዓይኖቼን እንቅልፍ የከለከላቸው አንድ አሳብ ገብቶኝ መኝታዬ ላይ ያገላብጠኛል። ሰዓቴን መለስ ቀለስ እያልኩ አያለሁ። አሜሪካ ውስጥ ዴንቨር ኮሎራዶ ትልቋ ልጃችን እምነትና ባለቤቷ ዮናስ በመጀመሪያ ልጃቸው በኖዋ (Noah ኖኅ እንደ ማለት) የተባረኩበት (የወለዱበት) እና እንደ ቤተሰብ ባለማዕረግ ያደረገንን አምላካችንን ስናመሰግነው የከረምንበት ጊዜ ነው። ኦ! ሌላም ደግሞ፣ የሁለተኛዋ ልጃችን የረቂቅን ከባድና ያልተጠበቀ ኦፕራስዮን በሚገርም የጌታ ትድግና በደህና ተሻግረነው ቤተሰባችን በትልቅ ምስጋና የከረመበት ወቅትም ነበር።

ረቂቅና ባለቤትዋ ዳዊት ደግሞ፣ ልሁልና መዝሙረ በተሰኙ ወንዶች ልጆች ተባርከው ስለነበር በዚያን ሰዓት ከአዲሱ ሕፃን ኖዋ ጋር ሦስት የልጅ ልጆች አቅፊን ለመሳም ጌታ አብቅቶናል። የድንቅ ሥራው መታሰቢያ አድርገን በመጨረሻ የሰጠን 'ትደነቅ ጥበቡ' ብለን ስም ያወጣንላት እጅግ የምንወዳት ልጃችንም ለበጋው ዕረፍት ትምህርት ቤቷ ስለተዘጋ ያለችው እዚሁ ዴንቨር ከእኔ ጋራ ነው። ዕንቅልፍ ባጣሁበት በዚህ ሌሊት አጠገቤ የሌለው ውድ ባለቤቴ ጥበቡ ኃይለሥላሴ ነው። ከልጆቻችንና በጌታ ከሆኑ ወገኖቻችን ጋር ዴንቨር ባለፋት አራት ሳምንታት የበረከት የአምልኮና እርስ በርስ የመጽናናት ጊዜ አሳልፈናል። አሁን ከእስራኤል ወደ አሜሪካ የመጣንበት የዕረፍታችን ማብቂያ ላይ ነን።

ከተባበሩት መንግሥታት ዓለም አቀፍ የሕፃናት እርዳታ ድርጅት (ዩኒሴፍ) በተሰጠው የሥራ ኃላፊነት ምክንያት እኔና ጥበቡ ከልጃችን ከትደነቅ ጋር ኢየሩሳሌም ከተማ መኖር ከጀመርን አራት ዓመት ሆኖናል። ከአሜሪካው ዕረፍታችን ወደ እስራኤል ከመመለሳችን በፊት ጥበቡ የሚሳተፍበት ከፍተኛ የተባበሩት መንግሥታት ስብሰባ ካናዳ ውስጥ ለአንድ ሳምንት ይካሄድ ነበር፤ ኪንግስተን በምትባል ከተማ ኦገስት 20 ቀን 2007 የሚጀምር።

በሥራ ምክንያት ከአገር አገር በሚዘዋወርበት ጊዜ ሁሉ ጥበቡ በዚያ ያሉትን ቅዱሳን አግኝቶ ሕብረት ማድረግ በተከፈተለትም በር ሁሉ ማገልገልም ሆነ መገልገል ይወዳል። ስለዚህም የካናዳውን ስብሰባ መሥሪያ ቤቱ ሲያቅድ ጥበቡ ደግሞ ቶሮንቶ ከመጋቢ ዘካርያስ ጋር ተደዋውለው ከኪንግስተኑ ስብሰባ በፊት ባለው ቅዳሜ እና ከኪንግስተን መልስ የእሁድ አገልግሎት እንዲሰጥ አቅደዋል። ከአውሮፕላን እንደወረደ ወንድም ዘካርያስ በቀጥታ ወገኖች ተሰብስበው ወደ ሚጠብቁበት የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን ወስዶት የቅዳሜውን አገልግሎት ሰጥቷል።

መድረክ ላይ ከወጣ በኋላ ጥበቡ ለመስበክ የተዘጋጀበትን ርእስ መንፈስ ቅዱስ አስለውጦት የዕለቱን መልእክት "እግዚአብሔርን ለሚወዱት እንደሃሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን" በሚለው ሮሜ 8፡28 ላይ በተጠቀሰው ምንባብ ተመርኩዞ ይሰብካል። ጌታ ክፉ የሆኑ ሁኔታዎችን ሁሉ ለልጆቹ እንዴት ለበጎ እንዲለወጥ እንደሚያደርግ ከሕይወቱ ምስክርነት እያገናዘበ ከብዙዎች ልብ በማይጠፋ መንገድ ያቀርባል። "በሕይወቴ ጣልቃ እየገባ ጣልቃ እየገባ መንገዴን አቀና" የሚለውንም መዝሙር በኃለ መንፈስ አስዘመረ። ለጉባኤውም ታላቅ የበረከት ቀን ሆነላቸው።

ያን ቅዳሜ አገልግሎቱን እንደጨረሰ ከመጋቢ ዘካርያስና ከሌሎችም ወገኖች ጋር ሆነው

እራት እየበሉ ስልክ ደውሎ ስለነበረው የበረከት ጊዜ አካፈለኝ። አመሻሽቶም ተጨማሪ የጸሎት ጊዜ ለማድረግ ተስማምተው ከነመጋቢ ዘካርያስ ጋር ለማደር እንዳቀደ ነገረኝ። ከምሽቱ ወደ አራት ሰዓት ተኩል ለሁለተኛ ጊዜ ደውሎልኝ እሁድ ጠዋት የኪንግስተኑን በረራ እንደሚያደርግና እዚያ እንደደረሰ የሚያርፍበትን ሆቴልና ዝርዝሩን በስልክ ሊነግረኝ ተስማምተናል።

****

ኦገስት 19 እሁድ ጠዋት። ዴንቨር የኢትዮጵያ ኢቫንጀሊካል ቤተክርስቲያን በማለዳው የጸሎት ጊዜ ልዩ የጌታ መገኘት የመንፈስ ቅዱስም የማጽናናት ኃይል ይሰማኛል። በተለያዩ ርእሶች ኃይለኛ ጸሎት በጉባኤው ተካሂዷል። በአምልኮው ክፍለ ጊዜ በፓስተር እንደሻው የመጣው ቃል ከኢሳይያስ 43፥18 ነበረ።

> "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ የፊተኛውን ነገር አታስተውሉ የጥንቱንም ነገር አታስቡ። እነሆ አዲስ ነገርን አደርጋለሁ እርሱም አሁን ይበቅላል።...በምድረበዳ መንገድን በበረሀም ወንዞችን አደርጋለሁ።"

ጌታ እግዚአብሔር በዚህ ቃልና በመጣው መልእክት አማካይነት ብዙ ለልቤ ተናግሮኛል። በእኔና በጥበቡ ሕይወት ባለፉት ዓመታት ጌታ ያደረገውንና ለክብሩ ምስክር አድርጎ በየደረስንበት ስንናገር የኖርነውን አሰብኩ። አሁን ግን በዚህ ማለዳ ጌታ የሚለኝ፡- "እነሆ አዲስ ነገርን አደርጋለሁ እርሱም አሁን ይበቅላል።...በምድረበዳ መንገድን በበረሀም ወንዞችን አደርጋለሁ" ነው። በተለይ ደምቆና ጎልቶ ወደእኔ ይመጣ የነበረው ቃል፡- "...በምድረበዳ መንገድን በበረሀም ወንዞችን አደርጋለሁ" የሚለው ነበር። እስካሁን በዘመናችን ከገጠመን ምድረበዳና በረሀ ጌታ እግዚአብሔር ያወጣቸውን ድንቃ ድንቆች ያሳለፈንን አስገራሚ የሕይወት መንገድ እያሳየኝ ከእንግዲህ ለሚገጥመን ሁሉ ያለፈውን የሚያስረሳ አዲስ ነገር ሊያደርግ እንዳለው ተሰማኝ።

ጥበቡ ሁልጊዜ ከሆነ አውሮፕላን ማረፊያ ሲደርስ ወይንም ትራንዚት ላውንጅ ውስጥ አለዚያም አውሮፕላን ውስጥ ስፍራውን ከያዘ በኋላ ሞባይል ስልካችሁን አጥፉ ከመባሉ በፊት ይደውልልኛል። በጠበቅሁት ሰዓት አልደወለም፣ ከዚያም እስከ ምሽቱ። እኔም ደጋግሜ ሞባይሉ ላይ ብደውልለት ውጤት አልባ ሆኖብኝ አሁን ልቤ መታወክ ጀምሯል። ምናልባት የመስመር ችግር ሊኖር ይችላል በማለት ኢሜይል አደረግሁለት። አሁን በእርግጠኝነት ይደርሰዋል ብዬ ኮምፒዩተሬ ላይ ብዙ ቆየሁ። ዓይኖቼ እንቅልፍ ያጡበት ምክንያቱ ይሄ ነበር። ድንገትም በጉጉት ስጠባበቀው የነበረው ስልክ ጮኸ!

"እሰይ ጌታ ሆይ ተመስገን! ኢሜይሌን አግኝቶ ማለት ነው የኔ ውድ!" አልኩና ባስቸኳይ አንስቼ፡- "ሃሎ! ሃሎ!"

"ሃሎ! ሃሎ! ሊሼ! ፍስሐ ነኝ ከጥበቡ ጋር ሆነን ነው የምንደውልልሽ" (በቴሌ-ኮንፈረንስ መሆኑ ነው)

ዶ/ር ፍስሐ ጉርሜሳ የረዢም ዘመን ጓደኛችን ሲሆን ከባለቤቱ ከሶስና (ምንሽ) ዓለማየሁ ጋር አሜሪካ ውስጥ ፖርትላንድ ኦሬገን ይኖራሉ። እንዲያውም ጥበቡ ወደ ካናዳ ከመሄዱ ከአራት ቀን በፊት እነሱንና ሌሎቹን ጓደኞቻችንን አስግድ ሙላትንና ወይንሸት ኃይለማርያምን ሊያያቸው ለአንድ ሌሊት አዳር ወደ ፖርትላንድ ሄዷል...ብቻ ሁኔታውን ለመረዳት አእምሮዬ በሚራሯጥበት ቅጽበት ፈጽሞ ይሆናል ብዬ ያልጠበቅሁት የጥበቡ ለየት ያለ ድምጽ መጣ፡-

"ማሚዬ[1] አይዞሽ አትደንግጪ። እህ! . . .እህ!… ትንሽ ስላመመኝ ነው።እህ! . . . እህ!… ሆስፒታል አስተኝተውኝ ሐኪሞች ችግሩ ምን እንደሆን እየመረመሩ ነው።እህ! . . .እህ!… ፍስሐ ሐኪሞቹን ስላናገራቸው እኔ እንዳይደክመኝ እሱ ያስረዳሻል፡እህ! . . .እህ!…አታስቢ ብቻ ጸልዩ! እህ! . . .እህ!…"

ጆሮቼ በዚች የሌሊቶች ሌሊት የሚሰሙትን ለማመን ተሳናቸው።

"በኢየሱስ ክርስቶስ ስም! ዳዲዬ[1] የኔ ፍቅር! … ምንድነው? ምንስ ተፈጠረ?? አይዞህ! እኔ ባስቸኳይ እመጣለሁ! እሺ! አንተ እንዳይደክምህ ዝም በል! አንተ ዕረፍ…!"

በትናንትናውና በዚች ሌሊት መካከል የሆነውን ማገናዘብ ተሳነኝ።

"ሊሼ! አይዞሽ! አስቸኳይ እርዳታ ሊያገኝ በሚችልበት ቦታ ላይ ነው ያለው። . . . ያመመው ፓንክርያሱን/ቆሽቱን ሳይሆን አይቀርምና ኃይለኛ የህመም ስሜት ስለሚሰማው ስቃዩን ለማስታገስ ሲሉ አሁን ሙሉ ለሙሉ ያስተኙታል። እኔም ትኩረት እየጠበቅሁ ነው፤ ምናልባት እኩል እንደርስ ይሆናል። ሰንዱና ጥበቡም (እህቴና ባለቤቷ) ተነግሯቸው ከዲትሮይት ሚቺጋን ወደ ቶሮንቶ አሁን በመንዳት ላይ ናቸው። መጋቢ ዘካርያስና ሌሎች ወንድሞችም ከአጠገቡ አልተለዩም። እነሱንም በስልክ አናግሬያቸዋለሁ። ከሁሉ በላይ ደግሞ በጥብቅ እየተጸለየ ነው…።"

ከፍሲና ከምንሽ፣ ከአሴና ከወይኒ ጋር (በቴሌ-ኮንፈረንስ) አብረን ጸለይን። ስልኩን ዘግቼ በአምላኬ ፊት ተደፋሁ።

"ውዴ[1]! . . የኔ ጥበቡ! ከቤቱና ከምናፈቅረው ቤተሰቡ ርቆ በሄደበት ጠላት አግኝቶብኝ ይሆን? . . . ጌታዬና አምላኬ ሆይ! ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?! . . . እኮ እንዴት?! ማንም በሌለበት በምድረበዳ?!" "ጌታ ሆይ! ይህ ድንገቴ ለሞት የመጣ ነው እንዴ?"

ስል ጌታዬን በጸሎት ጠየቅሁት። እግዚአብሔር አምላክ ገና በሕይወታችን የሚፈጽማቸው ነገሮች እንዳሉና ገና ዘመንም እንደሚመጣ በግሌ አምን ነበር። ለዚህም ነው ድንጋጤ የወደቀብኝና በጊዜው አንደበቴ ላይ የመጡልኝን ቃላት ሳልመርጥ ወደ ጌታዬ የጮኽሁት። በዚች የጭንቅ ሌሊቱ አብሬው በሌለሁበት መታወኩም ሌላው ጭንቁ ነበር። ዳሩ የእኔ አጠገቡ መሆን ምን ሊፈይድለት? ሁሉን ቻዩ ጌታ አምላካችን ይድረስለት እንጂ!

"አሁን ባሪያህን ልትረዳው የምትችለው አምላኬና ጌታዬ አንተ ብቻ ነህ፤ … አምናለሁ አሁን አንተ በዚያ ነህ! በቃ! ያንተ መገኘት ብቻ አምላኬ ሆይ! ያንተ መገኘት ብቻ…. እርሱን ነው የምፈልገው፤ እኔንም እርዳኝ! … እዚያ አጠገቡ! እዚያ እንድሆንና ጭንቁን እንድካፈለው እርዳኝ! ውዴ፣ ፍቅሬ፣ ዳዲዬ! ካለበት አገር … በዚያ እንድገኝ ባስቸኳይ እርዳኝ!"

ድንገትም ፀጥታ ሆነ በውስጤ፤ ነፍሴን የገጠማትን ማዕበልና ወጀብ ፀጥ የሚያደርገው የአምላኬ መገኘት በዙሪያዬ ተሰማኝ። ፀጥታው ምልክቴ ነው፤ የልጅነቴ አምላክና ጌታዬ ባስለመደኝ መንገድ ይረዳኝ ዘንድ ወደኔ መጥቷል ማለት ነው። በዓይነ ሕሊናዬ ያለፈው ሳምንት እሁድ ኦገስት 12 ቀን ዴንቨር ጥበቡ ያስተላለፈውን መልእክት አሰብኩ፤ አዎ! … የጉባኤውን እምነት እንዴት ከፍ ያደረገ የእምነት ቃል ነበር ከውስጡ የወጣው!

አስታውሳለሁ፣ ጥበቡ በእንዲህ ያለ የጤና መናጋት ውስጥ በድንገት ከመውደቁ ከአሥር ቀናት በፊት ወንድማችን መጋቢ አሳየኸኝ በርኼ እዚያው ከናዳ ታሞ በሞትና በሕይወት መካከል ሆኖ ሳለ እንዲጸልዩ ከተነገራቸው ወገኖች መካከል የመጀመሪያዎቹ እኔና ጥበቡ ነበርን። ሁኔታውን

[1] በመጽሐፉ ውስጥ የምታገኟቸው "ዳዲ/ዬ"፣ "የኔ ውድ"፣ "ውዴ"… ፤ እነዚህ በዓመታቱ መካከል ባለቤቴን የጠራሁባቸው ስሞቹ ናቸው። "ማሚዬ" እና "ዳዲዬ" እኔና እሱ የምንጠራራባቸው የፍቅር ስሞቻችን ናቸው፤ ይህን ስም ለራሳችን ለምን እንዳወጣን መነሻ አለውና ስትደርሱበት ትረዱኛላችሁ።

በጸሎትና በቅርብ እንከታተል ነበር። የወንድም አሳየኸኝ ባለቤት እመቤት ከካሊፎርንያ በርራ አሳየኸኝ በሚታከምበት ሆስፒታል በደረሰችበት ቀን ሐኪሙ "የምነግርሽ ጥሩ ዜና የለኝም፤ ባለቤትሽ በአስጊ ሁኔታ ላይ ነው፤" በማለት እንዴት እንዳስደነገጣት ጥበቡ ሰማ። እጅግም ውስጡ አዘነ። እንደ ባለሙያም በሐኪሙ አባባል ተቆጥቶ፡- "ድሮስ ከሰው ምን መልካም ዜና እናገኛለን?! ብናገኝም እንኳ እኛ የምናምነው የአምላካችንን ሪፖርት ነው! አምላካችን ከሞትም ያስነሳል፤ ካስፈለገም ጠላት የዘረፋቸውን የሰውነት ክፍሎች ሁሉ እንኳ ይመልሳል!" እያለ የተናገረውን አስብኩ።

እንዲያውም ባለፈው እሁድ መልእክቱን ከማቅረቡ በፊት ጉባኤውን እየመራ ለወንድም አሳየኸኝ ጸልዮም ነበር። በዚያን ቀን ጥበቡ ያቀረበው መልእክት በእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት ላይ የተመሠረተ ነበርና ብዙዎች እስከ ዛሬ ከልባቸው የማይጠፋ መልእክት እንደሆነ ይናገራሉ።

በዚህ አገልግሎቱ ብቻ ሳይሆን ዘመኑን ሁሉ ጥበቡ ለእግዚአብሔር አሳብ የተሰጠ አገልጋይ እንደሆነ አውቃለሁ። በዚህም ምክንያት ሰይጣን ለበቀል ተሞልቶ ሲያደባ አግኝቶት ይሆን ብዬ አሰብኩ። ዲያብሎስም "ብቻውን በምድረ በዳ ስገጥመው እስቲ ይታያል! ማን ከዚህ የሞት ወጥመድ እንደሚያስጥለው?" እያለ የፎከረም መሰለኝ። እኔ ግን እግዚአብሔር ከጥበቡ ጋር በሕይወት እንደሚያገናኘን፣ በዚህ ሁኔታ በሞት እንደማይወሰድ ተረድቼ ከተደፋሁበት ከአምላኬ የምሕረት ዙፋን ሥር ተነሳሁ።

በመንፈሴም አስተዋልኩ። ምንም ዓይነት እርዳታ እንዳይደረግለት ብቻውን ሆቴል ውስጥም ሊያገኘው ይችል ነበር እኮ! ባየር ላይ "እዚህ ወራጅ አለ" በማይባልበት በአውሮፕላን ውስጥ ቢሆንስ?

በዚያው ሌሊት ፈጥኜ በጸሎት አብረውን ሊቆሙ ወደ ሚችሉ ወገኖች ሁሉ ደወልኩ። እንዲሁም እሥራኤል ለሚገኙት የተባበሩት መንግሥታት ዓለም አቀፍ የሕፃናት እርዳታ ድርጅት መሥሪያ ቤት ባልደረቦቹ አሳወቅኋቸው። ከኢየሩሳሌም አንስቶ ኒውዮርክ እስከሚገኘው ዋናው መሥሪያ ቤት ፈጣን እንቅስቃሴ ተጀመረ። "ለሥራ ጉዳይ በውጭ አገር እያለ ይህ ስለደረሰበት መሥሪያ ቤቱ ላንቺና ለትደነቅ ቶሮንቶ የሚያደርሳችሁ ትኬትና ቪዛ ያዘጋጃልና ባስቸኳይ ባጠገቡ ለመሆን ተዘጋጁ፤" የሚል መልእክት ላኩልኝ። በእውነቱ ደነቀኝ፤ ቀኑን ሙሉ ልቤን ሞልቶት የዋለውን "...በምድረ በዳ መንገድን፣ በረሀም ወንዞችን አደርጋለሁ፤" የሚለውን የጌታ ቃል አሰብኩ።

በብዙ መለኪያዎች ቶሮንቶ ለኛ ምድረ በዳ በረሀም ነው። ባይተዋር ነን፤ ከመኖርያ ቤታችን በብዙ ሺህ ማይልስ ይርቃል። ነገር ግን ብቻውን በምድረ በዳ እገጥመዋለሁ ብሎ ሰይጣን ያቀደውን እቅድ ጌታ ከንቱ አድርጎበት በሁለት ቀን ጊዜ ውስጥ የካናዳው በር ተከፈተ።

የካናዳው የቪዛ ቢሮ አሜሪካ ውስጥ ከሚገኝባቸው ከተማ አንዱ ዲትሮይት በመሆኑ ልጃችንን ትደነቅን ይዤ ከዴንቨር ወደ ዲትሮይት በረርኩ፤ እህቴ ስንዱና ባለቤቷ ዶ/ር መጋቢ ጥበቡ ከሚኖሩባት ከተማ ማለት ነው። ስንዱ አሁን ወደ ዲትሮይት እየነዳች ተመልሳለች፤ ባለቤቷ ግን ከእነመጋቢ ዘካርያስ ጋር ዳዲ አጠገብ ለመሆን ቶሮንቶ ቀርቷል። በስልክ ካወራነው ሌላ እህቴን እንዳገኘኋት በዓይኗ ያየቺውን የዳዲን ሁኔታ ነገራኛለች። ምሽቱን እህቴ ቤት አብረውን ለመጸለይ ለተሰባሰቡት ወገኖች በእምነትና በእውነት በልቤ ሞልቶ የተረፈውን በዚህ አስጨናቂ ነውጥ ውስጥ ለኔ መልህቅ የሆነኝን ቃል የኢሳ 43፥18 ምንባብ ነው ያካፈልኳቸው፤ "...በምድረበዳ መንገድን በረሀም ወንዞችን አደርጋለሁ፤" የሚለውን። ሁሉም ይህን ቃል አስቀድሞ በልቤ ያስቀመጠውንና

ቀድሞ የተጠነቀቀልኝን፣ በውስጤም እምነትና መጽናናት የሆነልኝን ጌታን አመሰገኑት።

ቀናት የሚፈጀው የካናዳው ቪዛ ባንዲት ቀን ውስጥ ተጠናቀቀ። "ለከፍተኛ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ስብሰባ ወደ ካናዳ የሄደው የሥራ ባልደረባችን በድንገትና በጠና ታሞ ቶሮንቶ ማውንት ሳይናይ ሆስፒታል ስለገባ ባለቤቱና ልጁ ባስቸኳይ ባጠገቡ እንዲገኙ አስፈላጊውን እርዳታ ሁሉ አድርጉልን፤" በሚል ድርጅቱ ለኤምባሲው በጻፈው ደብዳቤ ምክንያት። ኒውዮርክ የሚገኘው ዋናው መሥሪያ ቤት ስለጥበቡ ጉዳይ ሃያ አራት ሰዓት የሚከታተል አንድ ቡድን አቋቋመ። ወድያውም "በየትኛውም ሰዓት ልትደውይልን ትችያለሽ አይዞሽ ሙሉ ለሙሉ ከጎንሽ ነን!" ሲሉ አበሰሩኝ።

ሆስፒታሉ የጥበቡን ሕይወት ለማትረፍ ለሚያደርገው ማንኛውም የሕክምና መረባረብ ሙሉ ኃላፊነቱን የሚረከብና ወጪውን የሚሸፍን ኢንሹራንስ ያለው ስለመሆኑም የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ባስቸኳይ ፋክስ ተደረገ። "...በምድረበዳ መንገድን በ በረሀም ወንዞችን አደርጋለሁ" የሚለው ትንቢታዊ ቃል በተግባር መገለጥ መጀመሩን አስተዋልኩ።

ልጄን ትደነቅን (ትዲ) ከእህቴና ከልጆቿ ጋር ትቼ ብቻዬን ወደ ቶሮንቶ ለመብረር ወሰንን። እነርሱ ትዲን ይዘው በሚቀጥለው አርብ ወደ ቶሮንቶ ይመጣሉ።

ማክሰኞ ኦገስት 21። ቶሮንቶ ካናዳ በሚያደርሰኝ አውሮፕላን ውስጥ **ነኝ። በምን** ሁኔታ ላይ ሆኖ ይሆን የኔን ውድ ጥበቡ የማየው?? የጠና ጉንፋን ይዞት የማያውቀው **ያ የእምነት** ሰው! ያ የእግዚአብሔር ሰው! ... "ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ጌታ ሆይ!" **እያልኩ ስብሰለሰል፣** ልቤ ሲርድ፣ እንባዬ ሲፈስ . . . በዘላለማዊው የእግዚአብሔር ቃል በመጽሐፍ **ቅዱሳችን ኢሳ** 43፡18 ላይ የሠፈረው ቃል በኃይል ወደ ልቤ ፈሰሰ፡

> "አዎን የኔ ጌታ አንተ የተራራ አምላክ ብቻ አይደለህም የም**ድረበዳም አምላኬ** ነህ! ባለፈው እኔንና ጥበቡን እንደረዳኸን ሁሉ ዛሬም ደግሞ በዚህኛው **ምድረበዳ መንገድን ...** በረሀውም ወንዞችን ታደርጋለህ አምንሃለሁ!"

የአውሮፕላኑ በረራ ረጂም አይደለም። በተለይም ዲትሮይት **ለቶሮንቶ በመኪና** የአራት ሰዓት መንገድ ነው። ቶሮንቶን ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ ዓይቻታለሁ። ዛሬ ግን **በቶሮንቶ አየር** ላይ ሆኜ ወደ ታች ስመለከት እነዚያ የገዘፉ ትላልቅ ሕንፃዎቿ ለዓይኔ ትናንሽ ሆነው **ታዩኝ፤ ገረመኝ።**

ውስጤም ይህን አለ፡- "ይህም ፈተና እንዲሁ ነው። ዛሬ እንዲህ በቤቴ **ገዝፎና** ሰማይ ጠቀስ ሆኖ ሊያስፈራራኝ ፊቴ የተደነቀረውን የከፋ ኃይል ዝቅዝቅ አየዋለሁ፤ ከ**ጫማዬ** በታችና ትንሽም ነው!" አልኩኝ። ልቤ እጅግ ድፍረትና አሸናፊነት እየተሰማው ሳለ ሊቀበሉኝ ከመጡቱ ወገኖቼ ከነመጋቢ ዘካርያስ ጋር ተገናኘን።

****

## "ወሳኝ ቀናት?!"

ማውንት ሳይናይ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል በቶሮንቶ የታወቀ ትልቅ ሆስፒታል ነው። ጥበቡ በመጀመሪያ የተወሰደው በአቅራቢያው ወደ ነበረ አንድ መለስተኛ **ሆስፒታል ነበረ። የሁኔታውን** ከባድነት ዓይተው ከቅማቸው በላይ ስለሆነ በአንቡላንስ ማውንት ሳይናይ **ሆስፒታል አደረሱ ገብቷል።** ጥበቡን በምን ዓይነት ሁኔታ እንደማገኘውና በእጅጉም ሊያስደነግጠኝ **እንደሚችል ያወቀው** ዶ/ር ፍሰሐ በቅድሚያ፡-

"እንደ ደረስሽ የምታያቸው በላዩ ላይ የተሰካኩትና በዙሪያው ያሉት ማሽኖች

*እንዳያስደነግጡሽ፤ መተንፈስ እንዲችል የመተንፈሻ መሣሪያ በጉሮሮው ገብቶለታል። ሥቃዩ እንዳይሰማውም አስተኝተውታል፤ አይናገርም..."*

እያለ በስልክ ከአሜሪካ ከመነሳቴ በፊት ያስረዳኝ እጅግ ጠቅሞኛል። ደግሞም ጌታ "ገና" ሲል ለልቤ ያረጋገጠልኝ የጥበቡና የኔ ነገር በዚህ እንደማያበቃ በሕይወት እንደማገኘው ጽናት ሆኖኛል። እንዲያ ባይሆን በዚያን ቀንና ከዚያም በኋላ ማውንት ሳይናይ ሆስፒታል የገጠመኝ ፈተና የእምነትን ትጥቅ የሚያስፈታ በሆነ ነበር።

የማውንት ሳይናይ አይሲዩ የሚገኘው 18ኛው ፎቅ ላይ ነው። ወደ ተኛበት ስገባ እነዚያን ሁሉ አስፈሪ የመሣሪያ ዓይነቶች አልፎ የሚሄድ እምነትና ተሻግሮ የሚያይ ልዩ ዓይን የተገጠመልኝ ያህል ነበር የሆንኩት። ብቻ ራሴን ያገኘሁት ወደ ጆሮው ተጠግቼ፦

*"መጥቻለሁ ዳዲዬ! ከሞት ጋር እንዳትስማማ! እነዚህ እግሮች ገና ይሄዳሉ! እነዚህ እጆች ገና ወደ ምስኪኖች ይዘረጋሉ። አትሞትም! በሕይወት ትኖራለህ የእግዚአብሔርንም ድንቅ ሥራ ትናገራለህ! ገና የእግዚአብሔርን ሥራ እንሠራለን!"*

በማለት ዓይኖቼ ከሚያዩት ያለፈ ነገር እየታየኝ በእምነት ስናገር ነበር! ወዲያው የእኔ መምጣት ተነግሮት ዶ/ር ክርስቲያን የተባለው የሳምንቱ ዋና የአይሲዩ ሐኪም ጥበቡ ስለሚገኝበት አጠቃላይ ሁኔታ ሊያስረዳኝ መጣ። ጓደኛችን ዶ/ር ፍስሐም ከኦሬገን በርሮ መጥቶ ቀደም ሲል ይኼንኑ ሐኪም አነጋግሮታል። ሐኪሙ የሚለውን ሁሉ አእምሮዬ ሊያስተናግደው ጉልበት እንደሌለው ስለሰጋ በአጠገቤ ሊሆን ወደ ሐኪሙ ይዞኝ ገባ። ተስፋዬ በአምላኬ ላይ የጸና ስለሆነ እኔንም አጸናኝ እንጂ ሐኪሙ ከሰባሰበው የምርመራ ውጤት ተነስቶ ሲናገር የጥበቡ ሕይወት ትልቅ አደጋ ላይ መሆኑን ነው የነገረኝ።

*"ፓንክርያሱ ክፉኛ ተጎድቷል፤ በዚህ ደረጃ የተጎዱ ሁሉ የመትረፍ እድላቸው ጥቂት ነው፤ ከአንግዲህ በሕይወት ለመኖሩ ወይንም ላለመኖሩ የሚቀጥሉት ቀናት "ወሳኝ ቀናት" ይሆናሉ፤ አሁን በጥንቃቄ የምንከታተለው የትልልቅ ኦርጋኖቹን ሁኔታ ነው። ባለቤትሽ ከተዋጠበት አስጊ ጥሻ ካልወጣ ሕይወቱ ከፍተኛ ችግር ላይ መሆኑን ልደብቅሽ አልችልምና አዝናለሁ..."*



ጥበቡ ከመታመሙ ከሦስት ቀናት በፊት

እኔ የሐኪሙን ሪፖርት አስታኮ ልቤን ሊያርድ የሚፈልገውን የሞት ድምፅ በመንፈሴ እየተቃወምኩ የሰማሁትን ላለመስማት ቆርጬ ተነሳሁ። በሕይወት ለመኖር ላለመኖር "ወሳኝ ይሆናሉ" ያላቸውን የሞት ጥላ ያጠላባቸውን ቀጣይ ቀናት በሕይወት እንዲያሻግርልን በጸሎት

በአምላካችን ፊት ቆምን! በቅርብና በሩቅ በዓለም ዙሪያም ያሉ ክርስቲያን ወገኖችም ዙሪያዬን እንደ አጥር በጸሎት ቆሙልኝ። ልጆቻችንና የልጅ ልጆቻችን የሃያ አንድ ቀኑ አራስ ሕፃን ኖዋ ሳይቀር ቤተሰቦቻችንና ጓደኞቻችን ከአሜሪካ ወደ ቶሮንቶ መጎብኘት ጀመሩ።

የጥበቡ ኃይለሥላሴ ሕይወት የሞት ጥላ እንዳንዣበበበት የእግዚአብሔር ሕዝብ በምድር ዙሪያ ሰማ፤ የሚያውቀው የማያውቀው። ቀደም ሲል እንደገለጽኩት የቅርብ ወንድማችን ጋ/ር አሳየኸኝም በተመሳሳይ ሁኔታ መታመሙን ሰምተን ከሚጸልዩት ወገኖች መኻል እኔና ጥበቡ ነበርን። ዛሬ ግን በጽኑ የሚጸለይልን እኛ ሆንናል።

የሽንፈትና የስንፍና ቃል ሲናገር ሰምቼ የማላውቀው ያ የእምነት አርበኛ ዛሬ በአይሲዩ ማሽኖች ታጥሮ ሂ ብሎ ተጋድሟል። የተሰካኩበትን መሣሪያዎች ድንገት ተወራጭቶ ከላዩ ላይ እንዳይነቃቀላቸው እጆቹና እግሮቹ ከአልጋው ጋር ታሥረዋል።

የእህቴ የሰንዱ ባለቤት የነገረኝን አስታውሳለሁ፦

"የሕመሙ ስቃይ እንዳይሰማው ሙሉ ለሙሉ የማስተኛ መድኃኒቱን ሲሰጡት፣ ጥበቡ ልክ ትልቅ ጉባኤ የሚመራ ሰው ይመስል በከፍተኛ ድምጽ እጆቹን እያወዛወዘ፦ የእግዚአብሔር ክንድ ሆይ ተነስ! የእግዚአብሔር ክንድ ሆይ ተነስ! ለእኛ!

ከጥንት የነበረው ያ ታላቅ ግሩም ኃይል ዛሬም ይንቀሳቀስ በእኛ! እያለ እየዘመረና እያስዘመረኝ ነው በመጨረሻ እንቅልፍ ውስጥ የገባው።"

ያ መረታትን የማያውቀው የኔን አንበሳና ተጋዳይ እንዲህ ሆኖ ማየት ልቋቋመው የማልችለው ጉዳይ ሆነብኝ። ግና አምላኬ ከዚህ ሁኔታ እስኪያወጣውና እስኪያወጣኝ ድረስ በትዕግስትና በእምነት ከመቆም ሌላ ምርጫ አልነበረኝም።

ባጭር ጊዜ ውስጥ የማውንት ሳይናይ ሆስፒታል አይሲዩ እንግዳ መቀበያ አዳራሽ በወገኖች ብዛት ተጨናነቀ። የእንግዳ መቀበያው አዳራሽ የብዙ ሕመምተኛ ቤተሰቦች ማቆያ ስፍራ ነው። የኛ ሕዝብ አይሎ ተቆጣጠረው እንጂ። ለብዙ ዘመን በጥሩ ጓደኝነት አብረን የኖርን እስክንመስል፣ በቀንና በማታ ለደቂቃ ብቻዬን እንዳልሆን እነ መጋቢ ዘካርያስ፣ መጋቢ ዓለማየሁና መጋቢ ኤፍሬም እንዲሁም በርካታ የቶሮንቶ ወገኖች አስደናቂ ጥንቃቄ ማድረጋቸውን ቀጠሉ። ምንጊዜም ውለታቸውን አልረሳውም። በተለይ ደግሞ መጋቢ ዘካርያስና ባለቤቱ ብዙ ውጥንቅጦች ከእግዚአብሔር አምላካችን እግር ስር እንዲወድቁ ደጉ አምላኬ ያዘጋጃቸው መሣሪያዎቹ ነበሩ።

****

*"ይህ ሰው ማን ነው?"*

በእኒያ ክፉ ቀናት መካከል አንዲት መልካም እህት እንዲህ አለች፦

"ቤት የእግዚአብሔር ነው! ... ይቺ እህታችን በዚህ ጭንቅ ውጥረት መሆኗ ሳይበቃት፣ የምታርፍበትና ራሷን የምታስገባበት ቤት በማጣት ግራ እንዳይገባት፣ እኔ ቤት ትረፍ! ሊጠይቋቸው ከአሜሪካም ሆነ ከሌላ አገር የሚመጡትን እንግዶቿንም ትቀበልበት።"

ቃሏንም በተግባሯ ገለጸች፤ 'በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን' የሚል ጥቅስ የተንጠለጠለበትን የቤት ቁልፏን ለመጋቢ ዘካርያስ ሰጠች።

እኔ ከአይሲዩ ርቄ መሄድ አሻፈረኝ ስላልኩ ነው እንጂ ይህም ብቻ አይደለም የቶሮንቶ

ወገኖች ያደረጉት። ለነገስ "እዚ ከሰው ጋር ካልሆነ ብቻዋን አትበላም !" የሚባል ነገር ከሚያውቁኝ ሰዎች ሰምተዋል። ስለሆነም እንደ ማንኛውም የምዕራቡ አገር የኑሮ ሩጫና የጊዜ ውድነት ባለው በቶሮንቶ ከተማ በቁርስ በምሳ በእራት አንዲት ቀን እንኳ ብቻዬን አልተውኝም። የሚያመጡት ምግብ አብረን በልተንና ጠጥተን ተርፎን ማስቀመጫ ያው ፍሪጅ ጠቦ እስኪጣል በመድረሱ 'ተራ ገብተን እናምጣ' እስከማለት ተደረሰ።

ስለ ምግብ ከነሳሁ ዘንዳ በፈረንጅ አገር የባህላችንን ምርጥ ምግብ 'ጥሬ ሥጋ' እንኳ አይቀርባችሁ የተባልን ይመስል ነበር፤ ያውም ሆስፒታል ውስጥ አይሲዩ ክፍል። የረዥም ጊዜ ጓደኛችን የሆነው ዶ/ር ምስጋናው ከ45 ደቂቃ በላይ ብስክሌት እየነዳ ከሚኖርበት ሩቅ ሰፍራ ጥሬ ሥጋ፤ እርሱ ራሱ ከቀመመው ድልህና ሰናፍጭ፤ ከስለታም ቢላዎች ጋር ይዞ መጣ። አንድ ባንድ እጆቻችንን ይዞ ወደ አንድ ክፍል አስገብቶን እንዲህ ሲል ተናገረ፡-

"ወንድሜ በዚህ ሁኔታ እንደማይሞት ከአይሲዩም በደህና እንደሚወጣ ጌታ ተናግሮኛልና እጅግ ደስ ብሎኛል ! ይህን ሥጋ ከሩቅ ድረስ ተሸክሜ የመጣሁት ለጌታ ምሥጋና ለማቅረብ ነውና እዚሁ ቁጭ ብላችሁ ካልበላችሁ በጣም አዝናለሁ !"

እርስ በርስ ተያየን ! እንዳንዶቻችን በተለይም እኔ፤ በእንደዚህ ያለ ሁኔታ ውስጥ ሆኜ ቀርቶ በደህናውም ጊዜ ለጥሬ ሥጋ ግድ የለኝም። ነገር ግን ከዶ/ር ምስጋናው ግሬት ማንም ሊያመልጥ አልቻለም። ሆስፒታል ውስጥ ያውም አይሲዩ ጥሬ ሥጋ ! የነገሩን አይቀሬነት የተመለከተው ፓስተር ዘካርያስ፡-

"ነበዝ ! በሉ እንግዲህ የማይቀር ጉዳይ ከሆነ ያለንበት ክፍል በቁልፍ በደንብ ይቆለፍ ! ሐኪሞች ወይ ነርሶች ድንገት መጥተው ይሄን ጥሬ ሥጋ ቢያዩ የጎደለ በሽተኛ ካለ ብለው ሰው ቆጠራ እንዳይሄዱ ! ደግሞም ከበላን በኋላ፣ አንድም ትርፍራፊ እዚህ ሆስፒታል ቆሻሻ መጣያ ውስጥ እንዳንጥል ! ልቅምቅም አድርጌ ከዚህ ጊቢ ውጪ እኔ ራሴ ይገፍ መውጣት አለብኝ !"

የመጋቢ ዘካርያስ ስጋትና አባባል በዚያች ክፍል በዶ/ር ምስጋናው አስገዳጅነት ተሰብስበን የነበርነውን ሁላችንንም እስክንፈራፈር አሳቀን ! ድንገትም ሳናውቀው በላያችን አጥልቶ የነበረውን የኃዘን ደመና ገፈፈና ሳቅ በሳቅ አደረገን፤ (በዋልድባም ይዘፈናል' እንዲሉ)።

በኢትዮጵያና በሌላም አገር የሚገኙ የሥጋ ዘመዶቹ ቶሮንቶ ውስጥ የሚኖሩትን ልጆቻቸውን "እባካችሁ ! ሊሻን በማታውቀው ከተማ ከፍተኛና ድንገተኛ ኃዘን ላይ ወድቃለችና ድረሱላት፣ ከጎኗ ቁሙላት !" ተብለው ተደናግጠው ሲመጡ በእግዚአብሔር ሕዝብ ተከብቤ አግኝተውኝ በመደነቅ ተሞልተዋል። ስድስት ወራት በፈጀ የቶሮንቶ የሆስፒታል ቆይታችን አንዳንዴ እምቢ ብዬ ካላደርኩ በቀር (እሱም በጣት ይቆጠራል !) ጥበቡ አንዲትም ሌሊት እንኳ ያለ ሰው ብቻውን አላደረም። ሌላው ቀርቶ "እኛ በተሻለ ሁኔታ ልንረዳው እንችላለን" በማለት በርካታ የቊንቅ ሌሊቶች ከጥበቡ ጋር ያሳለፉ ክርስቲያን ነርሶችና የጤና ባለሞያዎች ብዙ ነበሩ።

ስለሆነም ከቶሮንቶ ካናዳ አልፎ ከአሜሪካ ድረስ የሚመጡ ቤተሰቦቻችንና ጓደኞቻችን ያስታማሚዎቻችን ብዛትና ፍቅር፣ የሆስፒታሉን ሰራተኞች አስደነቀ። አልፎም *"ይህ ሰው ማነው? . . . የከተማው ነዋሪ ሳይሆን ይሄ ሁሉ ጠያቂስ እንዴት ሊያውቀው ቻለ?"* አሰኛቸው።

ጥበቡን ለመጠየቅ እኔንም 'አይዞሽ' ለማለት ይህ ሁሉ ሰው መጉረፉ በእርግጥ የሆስፒታሉን ሰራተኞች አስገርሟል። ከዚያ በላይ ግን ያ አጋጣሚ፡- በከተማው ውስጥ ለዓመታት ያልተያዩ

ወገኖች እንዲተያዩ፣ ተቃቅረው የነበሩ ይቅር ተባብለው በክርስቶስ ፍቅር እጅ ለጅ እንዲያያዙ፣ ሆስፒታሉ ወደ ጸሎት፣ ምልጃና እርስ በርስ የመጽናኛ ስፍራ መለወጡ ሌላው ለብዙዎች ድንቅ የሆነ አጋጣሚ ነበር።

የእግዚአብሔር ባርኮቱና ማጽናናቱ ቀጠለ።የሁሉ ገዢና አዛዥ የሆነው አምላካችን የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የፈሰሰውን የሕዝቡን ፍቅርና መስዋዕትነት እንደመልከም መዓዛ እያሸተተ በላያችን ያጠላብንን ጨለማ መግፈፍ ጀመረ። በዚህ ብቻ አላበቃም፤ ኒውዮርክ የሚገኘውም የጥበቡ ዋናው መሥሪያ ቤት ያደረገውን አስቸኳይ ውሳኔ በስልክ አስታወቀኝ፤ እንዲህ በማለት፡-

> "ከምድብ የሥራ ቦታውና ከመኖሪያ ቤታችሁ ርቃችሁ እንዲህ ያለ አጋጣሚ ስለደረሰባችሁ በጣም እናዝናለን። አንቺና ልጃችሁ ትደነቅ እስኪሻለው አጠገቡ እንድትሆኑለት ስለምንፈልግ የቀን አበል ተቆራጭ እንዲደረግላችሁ ተወስኗል። ሆስፒታሉ አቅራቢያ የሆነ ጥሩ ሆቴል ፈልጋችሁ ብትይዙ ምግባችሁንና መኝታችሁን ያለምንም ችግር ይሸፍንላችኋል። ትደነቅም የትምህርቷ ነገር ስለሚያሳስበን ወደ እስራኤል እስከትመለሱ ለጊዜው የምትማራቸውን ትምህርቶች ሊያስቀጥሏት የሚያስችሉ የግል (ፕራይቬት) አስተማሪዎች ፈልጊላት!"

ይሄ መቼም አስደናቂ ትድግና ነው።

በዚህ ወቅት ጥበቡ በዙሪያውና በውስጡም ስለሚካሄደው ጉዳይ **ምንም** የሚያውቀው ነገር የለም። በአምላኩ ክንድ ላይ አርፏል። አምላኩ እግዚአብሔር **ግን በዘመኑ** ሁሉ ሰዎችን ለማገልገል ፈጣን ለነበረው፣ ለሰዎች እንጂ ለራሱ ኖሮ **ለማያውቀው ለባሪያው**፣ የተባበሩት መንግሥታትም ጭምር እንዲያገለግሉት ልባቸውን አነሳሳ። ክርስቲያናዊ **አቋም ከሌለው** ዓለም አቀፍ ድርጅትና በእምነታቸው እኛን ከማይመስሉ ሰዎች ክብሩ አከብሮትና **ኃዘን ጋር "እባክሽን** በጣም እንደምንወደው 'እንደምንጸልይለትም' ንገሪልን" ሲሉ መስማት **የሚያስገርም ነበር**። የነገሥታትን ልብ እንደቦይ ውሃ በፈቱ ወደ ፈለገው የሚያዘነብል፣ የሥጋ ለባሽም ሁሉ ጌታ **የሆነው እግዚአብሔር** አምላካችን በባሪያው ላይ ያደረገው ሞገስና መወደድ እኔና ቤቴ ለደረሰብን ኃዘንና ስብራት ጠገንና መጽናናት ሆነልን።

የመጀመሪያዎቹ የአይሲዩ ቀናት ከባድ ነበሩ፤ እግዚአብሔር በመኻል ጣልቃ እየገባ የተስፋና የሰላም ጮራን እንዲህ ስለሚፈነጥቅባቸው ነው እንጂ። ተደጋጋሚ የሞት ድምፅ ከሐኪሞቹ በሰማን ቁጥር አስቸኳይ የጸሎትና የምልጃ ጥያቄዎች አብረውን ለቆሙ ሁሉ እንበትን ነበር። የቅርቡም የሩቁም ባንዴ ይስማማና ሁሉም በያለበት ወደ እግዚአብሔር ማደሪያ ጥበቡን ይዞ ይቀርብ ነበር። ስለ ጥበቡ ካላቸው ጥልቅ ፍቅር የተነሳ በአገልግሎትና በእድሜ የበሰሉት ጭምር እግዚአብሔርን በጸሎት የሚያሳስቡባቸው ቃላት ከአምላካቸው ጋር ሳይሆን ከሰው ጋር ሙግት የገጠሙ ይመስሉ ነበር። አንዳንዶቹን አገላለጦች ላመልከት፡-

- "እባክህ ጌታ ሆይ! ሰው አታሳጣን!"
- ". . . . . . አባት ያስፈልገናልና...እዘንልን!"
- ". . . . . ይግባኝ ብለናል ጌታ ሆይ በምሕረትህ አንተ ፍረድልን!" በማለት እግዚአብሔርን የተማጸኑ ነበሩ።
- "ጌታ ሆይ! በራሴና በቤቴ ላይ እስከዛሬ የደረሰውን ፈተና በትዕግሥት ተቀብያለሁ፡ ጥበቡን በሚመለከት ግን የጠላታችን ምኞት ይመስለኛልና አትቀበለው . . . ዋ!

ጌታ ሆይ! . . . ልንቀበለው የማንችለው ኀዘን ይሆንብናልና ዝም አትበለን!" እስከትል ድረስ ልቧ የተሰበረባት አንዷ የቅርብ እህታችን ነበረች።

• "ጌታ ሆይ አባክህ ጥበቡን አትውሰድብን እሱ ለቤትህ ይጠቅምሃል! እሱን ከምትወስደው እባክህ እኔን ውሰደኝ" ሲል የጸለየው ሌላው የቅርብ ጓደኛችን ነው። ጓደኛችን ይህን ጸሎት በእንባ ተሞልቶ ሲጸልይ መንገድ ላይ ከሁለት ወንዶች ልጆቹ ጋር መኪና ውስጥ ሆኖ ነበር። በጸሎቱ የደነገጡት ልጆቹ "ተው! ተው! እንጂ አባታችን! አሁን የጸለይከው ጸሎት እኮ ልክ አይደለም!" ሲሉት ነበር ወደ ልቡ የተመለሰው። "ለካስ እነሱ ደግሞ የኔ ልጆች ስለሆኑ አባታቸው እንዳልሞትባቸው ጸሎቴን ማረማቸው ኖሯል!" ሲል ነገረኝ።

በወንድም ሳሙኤል ኃይሉ መሪነት በምድራችን ለሚካሄደው አገር አቀፍና አህጉር አቀፍ ትላልቅ ወሳኝ ጉዳዮች የሚጸልዩ የጸሎት አገልጋዮች እንዳሉ ይታወቃል። በልዑል ጌታ በእግዚአብሔር ፊት ማላጆች አድርጎ ያስነሳቸው የአርባና የ21 ቀናት ጾም ጸሎትን ያለማመዳቸው ወገኖች ናቸው። መንፈስ ቅዱስ በተደጋጋሚ በእነዚህ ማላጆች ስለጥበቡ በጥብቅ እንዲጸለይ አድርጓል። እግዚአብሔር አምላክ ጥበቡን ሊወስደውና ከምድር ኑሮው ሊያሳርፈው እንዳሰበ ከገባቸው መካከል አንደኞቹ እነሱ ነበሩ። ሆኖም እንደመረዳታቸው መጠን ግን ልባቸው አልችል ስላለባቸው፡- "እግዚአብሔር ሆይ! ልትወስደው ብትፈልግ እንኳ ለእኛ ስትል ተውልን!" ሲሉ መጸለያቸውን ሰምቼ ልቤ ተነክቷል።

በሥራቸው ዓለምም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው መልካም ምሳሌነታቸውን ትተውልን ወደዘላለም ቤታቸው ቀድመውን የተሻገሩ የቅርብ ጓደኞቻችን አሉ። እነ ዶ/ር ሚልክያስ ሻሜቦ፣ ሳይንቲስት/ፊዚስት ተወልደ ዮሐንስና ዶ/ር ብርሃኑ ሀብቴ። ከእነዚህ ከሶስቱም ጋር ጥበቡ የሚያስታውሳቸውና እንስቶ የማይጠግባቸው ትዝታዎች አሉት። በተለይ ተወልደና ብርሃኑ በድንገት የተለዩን ጥበቡ ካናዳ ሆስፒታል በነበረበት ወቅት ነበረ። እንኳን ለእሱ ሊነገር፣ ለእኔም ተደብቆ ቆይቶ አሜሪካ ከገባን ወዲያ ነው የተነገረኝ። በተለይም የቅርቡ ከነበረው ከዶ/ር ብርሃኑ የመለየት ሃዘኑ ያላገገመው ፕሮፌሰር አታላይ ዓለም ሊጠይቀን ዴንቨር መጥቶ የሆነውን አልረሳውም። በናይን ከተማ አንድ ልጇ ሞቶባት ልትቀብር በጉዞ ላይ ለነበረች ለዚያች መበለት ጌታ "እራራላት" (ሉቃ 7፡11-15) የሚለውን ቃል አካፈለን። ሴትዮዋ ልጄን አስነሳልኝ ብላ ጌታን ስትለምነው እንኳ ዓይታይም፤ እርሱ ግን እራራላት! "ጌታ ሆይ ለእኛም አባክህ እራራልን.... እራራልን! እንዴት ያለምሳሌ ትተወናለህ?" ፕሮፌሰር አታላይ ብሶቱን፣ መሳሳቱን፣ ጥልቅ ኃዘኑን፣ . . ስቅስቅ እያለ በጌታ ፊት በማልቀስ የገለጸበት ቃል ነበር። በኃዘን የቆሰለው ልቡ ገና ሳይሽር ይሄኛውም እንዳይደገምበት ጣልቃ ሊገባልን በሚቻለው ጌታ ፊት የነፍሱን ሰቆቃ አፈሰሰው!

◆◆◆

*"ሕመም የሚቋቋም ዘረ-መል!" ወይንስ ...?*

በተመሳሳይ ሁኔታ እዚያው አይሲዩ ጥበቡ አልጋ ዙሪያ እንዲሁም በእንግዶች መቀበያው አዳራሽ የሚካሄደው ጸሎት አስገራሚ ነበር። ጥበቡ ለቀናት አሁንም የመሣሪያ ዓይነቶች ሁሉ በላዩ እንደተደረጉ ናቸው። በዙሪያው እየተካሄደ ስላለው ጉዳይ አያውቅም። የሐኪሞቹንም የየዕለት ገለጻ ከተቀበልነው አንዳችም ተስፋን የሚያነሳሳ አልነበረም። እኛ ግን ሐኪሞቹና ነርሶቹ ሥራቸውን ሲያገባድዱ ለጸሎት በአልጋው ዙሪያ እንቆማለን። የሕክምና ባለሞያዎቹም ያውቃሉ ይሄን እንደምናደርግና ጸሎት ላይ ከሆንን አጣዳፊ ጉዳይ ካልሆነ እስክንጨርስ ይጠብቁናል። "አብርሃም

ተስፋ ባልሆነው ጊዜ ተስፋን ይዞ አመነ" (ሮሜ 4፡18) እንደሚል ቃሉ የጥበቡ ሁኔታዎች ሁሉ ተስፋ ባልሰጡን ጊዜ እግዚአብሔር በቃሉ የሰጠንን ተስፋ ይዘን ቆምን።

ከእነዚህ ባንዱ ቀን ለመጀመሪያ ጊዜ ተስፋችንን የሚያለመልም ዜና ተገኘ! ልጆቻችን መጥተዋል ከአሜሪካ፤ የሐኪም ሪፖርት የምንሰማበት ወቅት ነው። ዛሬ ሪፖርቱን ሊያሰማን የሰበሰበን የአይሲዩ ዋና ሐኪም ዶ/ር ዋከስ ነው። ንግግሩን ሲጀምር እንዲህ አለን፡-

> "ዛሬ የዶ/ር ጥበቡ ኃይለሥላሴ ደህንነት ወደ ምንፈልገው አቅጣጫ እየተቀየረ መሆኑን ልነግራችሁ እወዳለሁ። ምክንያቱን በውል አላውቅም! ሕመም መቋቋም የሚችል ጥሩ ጂን (ዘረ-መል) ስላለው ይሁን ወይንም ገዘም ብሎ እድል . . ወይንም የምታደርጉት ጸሎት...አላውቅም! ብቻ የምናደርጋቸው የምርመራ ውጤቶችችን ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያመለክቱን... ሁኔታው ወደ ጥሩ አቅጣጫ እየተለወጠ መሆኑን ነው!"

እኛም በደስታ ሲቃ ተሞልተን፡-

> "አይ! የደህንነቱን አቅጣጫ ወደመልካም የለወጠው የጸሎት ኃይል ነው! የጸሎት ኃይል ነው!" አልነው። ሐኪሙም መልሶ፡- "አዎን! አዎን! አውቃለሁ! እሱን ማድረግ ቀጥሉ!"

አለን። በላያችን ለቀናት ከብዶብን የነበረውን የኀዘን ደመና ጌታ በዚያን ቀን ገፈፈልን! ከዚያን ቀን ወዲያ የጤናው ሁኔታ እየተሻሻለ መጣና ለ15 ቀናት ከነበረበት አስጊ ሁኔታ ጥበቡ ነቃ! ሐኪሞቹ በውስጡ አገኘን በሚሉት ዘረ-መል ሳቢያ ወይንስ የእግዚአብሔር ሰዎች ጸሎት ውጤት!?

****

*ሴፕቴምበር 4 2007።*

በላዩ ላይ የተሰካኩት መሣሪያዎች ተነስተው ለመጀመሪያ ጊዜ ዓይኖቹ ተገልጠው ዓይኖቻችንን አዩ! ደስታችን እጅግ ብዙ ነበር! አጠገቡ የነበርነው እኔና እህቴ ስንዱ ነበርን። ታስረው በነበሩት እጆቹ አቅፎ ሊስመን በቃን! ስንዴ ወደ አይሲዩ አዳራሽ የምሥራቹን ለመንገር ሮጠች። ከ19 ዓመታት በኋላ ሴፕቴምበር 4 ለቤተሰባችን የሃሴትና የደስታ ቀን ሆኖ ታሪክን እንዲደግም የቀናች ሁሉ ጌታ እግዚአብሔር ምሕረት አደረገልን።

ከጥበቡ ጋር ሶማሊያ ለ11 ዓመታት አብሮት የታሰረው ልጃችን ኢያሱም ሰሞኑን አብሮን አለ። ከአሜሪካ መጥቶ እንግዶች መቀበያ ክፍል ከነበሩት ወገኖች መካል ነበር። "ጌታ ሆይ እንዴት ዳዲን በዚህ ሁኔታ ትቼው ምንም ለውጥ ሳላይ እሄዳለሁ?" እያለ በጸሎት ሆኖ ሲያለቅስ ነው ስንዱ ይህን የምሥራች ያበሰረቺው።

ሶማሊያ በግፍ ለ11 ዓመታት የዘጋችባቸውን አስጨናቂ በር አምላካችን ሰባብሮ ጥበቡንና ኢያሱን ከእኔና ከልጆቻችን ጋራ በድል ያገናኘን ቀን ሴፕቴምበር 4/1988 ነበረ። ዛሬ ደግሞ ከ19 ዓመታት በኋላ በዚያቹው በማንረሳት የድል ቀን ሌላ ድል ለቤተሰባችን ጨመረልን። ኢያሱ የምላ ግብዣ ስለነበረው ጋባዦቹ ከሆስፒታል ሊወስዱት ቢመጡ የኢያሱ መልስ አጭር ነበር፡- "ይቅርታ አድርጉልኝ ይሄን ተአምር ትቼ የትም አልሄድም!"

ጥበቡ እኛን እያቀፈ ቢስመንም የመድኃኒቱ ኃይል ገና የከረመበትን ሁኔታ እንዲያገናዝብ አላደረገውም ነበር። ድምጹም ገና በደንብ ጎልቶ አይሰማም። ግን ነቅቷል! "ጉባኤው ተሰብስቦ ይጠብቀናል! እንሂድ እንጂ! ...እዚህ ምን እናደርጋለን...." ጥበቡ እንደበቱን የከፈተበት

የመጀመሪያ ንግግሩ ነበረ። በሕመም ቢሆን በጤና፣ በማታ ቢሆን በቀን. . የጥበቡን ልብ የሞላው የእግዚአብሔር ሥራና ቅዱስ ጉባኤው እንደሆነ ከዚህ የበለጠ ምን ምስክር አለ? !

****

*የዮሐንስ ነገር!*

ዮሐንስ - የቶሮንቶ ወገኖች ጆኒ ይሉታል። ጥበቡ ሆስፒታል ከገባበት ከመጀመሪያው ጊዜ አንስቶ ለዳዲ የሚደረግለትን እያንዳንዱን ነገር በጥንቃቄና በንቃት ይከታተላል። ሐኪሞቹም ሆነ ነርሶቹ በልባቸው እንዲያው አንድ የሆነ ባይተዋር እንግዳ ሰው የሚያከሙ ብቻ እንዳይመስላቸው፣ ''He is my Dad & I am a Nurse!'' ይላቸዋል። ጆኒና ዳዲ የተገናኙት በሶማሊያው የ11 ዓመት የምርኮ ዘመን መጀመሪያ ላይ ነው። ጥበቡ ከሳደጋቸውና ከስተማራቸውም ልጆች መካከል አንዱ ነው። በአስገራሚ ጥበብና ተጋድሎ በዳዲ አስተባበሪነት በሶማሊያው እስር ቤት ተምረው 12ኛን አጠናቀው ከወጡት ኀበዝ ተማሪዎቹ መኻልም አንዱ ነው። ጆኒ ስለዳዲ የሚናገረው ብዙ አለው።

"ለእኔ ዶክተር ጥበቡ ሦስት ነገሮች ነበር። አባቴ ነበር። ከ6 ዓመት ጀምሮ አሳድጎኛል። አስተማሪዬ ነበር። ከ1-12ኛ ክፍል አስተምሮኛል። ዛሬ እሱ ያስተማረኝ ትምህርት መሠረት ሆኖኝ ነው ካናዳ ውስጥ ፕሮፌሽናል ነርስ ብቻ ሳልሆን የነርሶችም አስተማሪ ለመሆን የበቃሁት። ሶስተኛ ነገር ሐኪሜ ነበር። እስር ቤት ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ ሁለት ጊዜ ሞት አፋፍ ደርሼ ነበር፣ ዛሬ በሕይወት ኖሬ ለዚህ የበቃሁት በአባቴ በዶ/ር ጥበቡ ጥረት ነው፤" የሚለው ምስክርነቱ ዋናው ነዉ።



ዮሐንስና ጥበቡ በቶሮንቶ ካናዳ 1995 እ.ኤ.አ

ጆኒ ከማይረሳቸውና እግዚአብሔር በዳዲ ተጠቅሞ ሕይወቱን እንዴትና እንዴት እንዳተረፈለትም ያስታውሳል፤ እንዲህ በማለት፡-

"አንድ ቀን በድንገት አንገቴ ላይ በፍጥነት እያደገ የሚሄድ እባጭ (እጢ) ገጠመኝ። "እባጩ በአንገቱ ወስጥ ለውስጥ የሚያድግና ጉሮሮው ውስጥ ፈንድቶ የሚገድለው ነው" ተባለ። ትዝ የሚለኝ ግን ስለዚህ ሕመሜ ዶክተር ብዙ መጸለዩ ነው። እናም 'በመገለጥ' ይመስለኛል ይሄን ያገኘው ሦስት አንቲባዮቲክሶች ወስዶ አንድ ላይ ቀላቀላቸው። ቴትራሳይክሊን አምፒሲሊን ፔኒሲሊን የተባሉትን። ጸለየና በእባጩ ላይ ደመድሞ በፋሻ አሰረልኝ። በማግስቱ የታየው ተአምር ነው። እባጩ ከሰውነቴ ሁሉ ተሰብስቦና አፍ አውጥቶ ከውስጡ ያዘለውን ወደ ውጭ ማፍሰስ ጀምሮ ተገኘ። ያው ምንም ዓይነት ማደንዘዣ በሌለበት እስር ቤት የበሽታውን ሰንኮፍ ከውስጡ ጨርሶ ለማውጣት በጊዜው ምንም ዓይነት አማራጭ አልነበረውም። እንዳልወራጭ እጆቼንና እግሮቼን በሰዎች አስይዞ ያን ተሰብስቦ የቆረዘዘውን እባጭ አፍረጥርጦ ማውጣት ነበረበት። እንደ ኀድጓዳ ሳህን ሙሉ መግል ነገር ነበር ከዚያ እባጭ አፍረጥርጦ ያወጣው። ያን አንቲባዮቲክስ

እንደገና በዚያ አንገቴ ላይ አሁንም ጸልዮ ደመደመና አስሮልኝ አደረ። በሚቀጥለው ቀን ከእባቄ ነፃ የሆነ ንጹህ አንገት ኖረኝ! አባቴ እኔን ለማትረፍ በደረገው ጥረት ይኸው በሕይወት ኖሬ ለመመስከር በቃሁ።" ጆኒ በዚያው በሶማሊያ እስር ቤት ሳሉ ገጥሞት የነበረውን ሌላ አደገኛ የጤንነት ችግር እንዲህ ሲል ይመሰክራል፡-

"በሌላ ጊዜ ደግሞ የአሥራሁለት ዓመት ልጅ እያለሁ ነው። ሰውነቴን በአደገኛ ሁኔታ ላይ የጣለ እጅግ ዝቅተኛ የሆነ የደም ግፊት ችግር (low blood preasure) ገጠመኝ። ከዚህም የተነሳ ሰውነቴ እጅግ በዙ የሆነ ወሃ ከምችት ያጠራቅም ገባ። ከላይ እስከታች ሰውነቴ ሊፈነዳ እንደደረሰ ፊኛ ወይንም ባሉን ተነፋ! እንኳንስ እንዲህ ላለው ከፍተኛ ችግር ቀርቶ፣ ለቀላሉም ሕመም ማስታገሻ መድኃኒት ማግኘት በማይቻል በዚያው አስጨናቂ ሁኔታ ውስጥ ዶ/ር ጥበቡ ትገዘ የሚለኝ ነገር ቢኖር ሲጸልይ ማደሩ ነው። በሚቀጥለው ቀን የወሀኒውን ወታደሮች ከእስር ቤት ውጪ ሰዎችን እንዲያከም ይዘውት ሲወጡ የበሬ ጉበት ይዞልኝ መጣ። በወጣ ቁጥር ያን ጉበት እየያዘ በማምጣት በብዛት ይመገበኝ ጀመር። ያ የውሃ ከምችት ባጭር ጊዜ ውስጥ ከሰውነቴ ሙጥጥ ብሎ ተወገደልኝ።"

ዛሬ ደግሞ ቶሮንቶ ካናዳ ውስጥ ጆኒን ነርስ አድርጎት፣ በተራው ብድር ከፋይ ያደረገው የእግዚአብሔር አሠራር ይገርመኛል። ቢያስፈልግ እንዲሚገትለት የጤና ባለሞያና የልጅ አስታማሚ አድርጎ በአይሲዩ ምድረበዳ ጆኒን ከአባቱ ጋር አገናኘው! በተለይ ደግሞ ለኔ አይሲዩ ውስጥ ዳዲ ላይ ተሰካክተው የነበሩት የመሣሪያ ዓይነቶች ምንነታቸውን ለሚጠይቀው አእምሮዬ ጆኒ መልስ እየሰጠ አሳርፎኛል። በመቆጣጠሪያው ላይ የሚታዩትን ቁጥሮች ከፍታቸውንና ዝቅታቸውን ከነትርጉማቸው የሚያብራራልኝ ጆኒ ነበር።

ጆኒ በልጅነቱ እስር ቤት ሳለ ከገጠሙት መራር ገጠመኞች ሌላ ከዳዲ ጋር በተገናኘ ፈገግ የሚያደርግ ትዝታም አለው፤ እንዲህ ይተርከዋል፡-

"ዶክተር ጥበቡ እስር ቤት ሰውስጥ ሳለንም በጸሎት ይተጋ ነበር። ሲጸልይ ደግሞ እንደ ልማድ በጣም ይጮኽል። ብዙ ጊዜ ሲጸልይ ደግሞ "ሃሌ ሉያ!" ማለትን ያበዛል። በአጋጣሚ እኛ ካለንበት ራቅ ብሎ ያለ አንድ ስሙ "አሊ ዩያ" የሚባል ሙስሊም ሰው ነበረ። እና አንድ መንከር የሚባል ተንኮለኛ ሰው ነበረና ወደዚያ ሙስሊም ሰውዬ ሄዶ፡- "አሊ ዩያ፤ ዛሬ ዶክተሩ ምን እንደነካው አይታወቅም! አሊዩያ እያለ ይጮሃል፤ ፈልጎህ እንደሆነ እስቲ ሂድለት እየጮኸ ነው!" ይለዋል፤ ሰውዬውን ከተኛበት ከእንቅልፉ ቀስቅሶ። አሊ ዩያም እውነት መስሎት ወደዶክተር መጥቶ፡ "ምነው ዶክተር ፈልገኸኝ ነበር አሉ" ይለዋል። ዶክተር ወጣና በዚያ በማልረሳው ፈገግታው፡- "አልፈለግሁህም" አለው። ሁሉም ለቀልድ መሆኑን ሲያውቁት ተሳስቀው አለፉት።"

****

# 2

# የብርሃን ፍንጣቂ !

ጌታ እግዚአብሔር ጥበቡን ከሞት አፋፍ ነጥቆ ሰጠን። 60ኛ ዓመት የልደት በዓሉንም ከወገኖች ጋራ ሆስፒታል ውስጥ አከበርንለት። በዚህ ደረጃ የጥበቡ ጤንነት መሻሻል ከቀጠለ የከናዳው ቆይታችን በቶሎ ይደመደማል፤ ብለን ብዙዎቻችን ገመትን። ልጃችን ትደነቅ ወደ11ኛ ክፍል የምትገባበት ጊዜ ነበር። በዚያ ዓመት ለዩኒቨርሲቲ የሚያዘጋጃትን የኢንተርናሽናል ባክሎርየት (አይቢ) ክፍለ ትምህርት መውሰድ የምትጀምርበትም ጊዜ ነው። እንኳንስ ሦስት ሳምንት አንድ እንኳ ከትምህርት ገበታዋ መለየት የማትችልበት ጊዜ። አባትዋ ከአይሲዩና ከነበረበት አስጊ ሁኔታ ይውጣ እንጂ ተሽሎትና ከሆስፒታል ወጥተን ወደ እስራኤል የምንመለስበት ሁኔታ ሩቅ ነበር። ስለዚህም የትምህርቷ ነገር አሳሳቢ ጉዳይ ሆነና ከትደነቅ ጋር ጸለይን።

እግዚአብሔርም ሌላ አንድ አስደናቂ ቸርነት አደረገልን። ለመርዶክዮስና ለአይሁድ ሕዝብ ሐማ ካውጠነጠነው የሞት ፍርድ ይታደጋቸው ዘንድ ንጉሥ አርጤክስስን እንቅልፍ ነስቶ መዝገብ ሲያገላብጥ ያሳደረው ዓይነት ታሪክ ለእኛም ተደገመልን። የልጃችን የትምህርት ዘመን ሊስተጓጎል መሆኑን ያስተዋሉ የጥበቡን *መሥሪያ* ቤት ሰዎች እንቅልፍ እስኪያጡ ድረስ እንዲጨነቁ አደረገ።

ስለዚህም በመስከረም ወር መጨረሻ ስልክ ደወለው፡- "የልጃችሁ የትደነቅ ትምህርት እየተስተጓጎለ መሆኑ አሳስቦናል! ስለዚህ ባስቸኳይ ካናዳ ወይንም አሜሪካ የምትገባበት ትምህርት ቤት ፈልጊላትና አስታውቂን፤" አሉኝ። እኔም ምስጋናዬን ካቀረብኩላቸው በኋላ፡- "መቼም አሁን ካናዳ ያስቀመጠን የጥበቡ የጤንነት ጉዳይ ነው። አሜሪካ ከሆነ ግን ልጆቻችን እምነትና ረቂቅ እዚያ ስለሚኖሩ ከእህቶቿ ጋር ሆና እንድትማር እነሱጋ ብንፈልግላት ይሻላል፤" አልኳቸውና ውጤቱን ባስቸኳይ እንድገልጽላቸው ተስማማን።

የነርሱን ስልክ ዘግቼ ወዲያው ወደትልቋ ልጃችን ወደእምነት ደወልኩኝ። ደስታዋ እጅግ ብዙ ሆነ። "ማሚ ከትዲ ጋር እኮ እኔና ረቂቅ ብዙ ጊዜ አብሮ የመኖር እድል አልነበረንም። አሁን እንዴት ያለ ግሩም እድል እግዚአብሔር ሰጠን!?" አለች። በትዲ መወለድ እግዚአብሔር የባረከን ጥበቡ ከሶማሊያ ከተመለሰ በኋላ ስለሆነ በእርሷና በሁለቱ እህቶቿ መካከል የ14 እና የ15 ዓመት እድሜ ልዩነት ነበራቸው። እነርሱ ለኮሌጅ እድሜያቸው ሲደርሱ ትዲ ገና ትንሽና መዋዕለ ሕጻናት እንኳ ያልገባች ልጅ ነበረች። ስለዚህ ለእህቷ የሚሆን ጥሩ ትምህርት ቤት ወዲያው

ኢንተርኔት ገብታ ስትፈልግ ከእሷ ቤት በመኪና የ10 ደቂቃ መንገድ ርቀት ላይ የሚገኝ አንድ ዕውቅ እና ሰዎች ልጆቻቸውን በዚያ ለማስገባት በተጠባባቂነት የተመዘገቡበትን ተወዳጅ ትምህርት ቤት አገኘች። ወዲያውኑ የት/ቤቱን ዳይሬክተር ስልክ ደውላ ስታናግራት፣

"በእርግጥ ለ11ኛ ክፍል አንድ ቦታ ብቻ አለን፤ እሷን ነው መሰል የሚጠባበቀው። የውጭ ተማሪዎች ቪዛ እንድታገኝ የሚያስችላት አይ ትዌንቲ ለማግኘት በአብዛኛው ከ3 - 6 ወር ይጠይቃል። የሷን ግን በስፔሻል ኬዝ ባስቸኳይ የሚያልቀበትን መንገድ እንፈልጋለን፤" የሚል ነበር የዳይሬክተሯ ምላሽ። ስለትድዬም ትምህርት በገጠመን ጨለማ ውስጥ፣ የብርሃን ፍንጣቂን እግዚአብሔር አሳየን! እግዚአብሔር ይሄን ታላቅ ቸርነት አድርጎልን ከሚወዷትና ከምትወዳቸው እህቶቿ ጋር ትምህርቷን ለመቀጠል ወደአሜሪካ ሄደች። ይህ መጽሐፍ ከመታተሙ በፊት ልጃችን ትደነቅ የመጀመሪያ ዲግሪዋን በከፍተኛ ማዕረግ አጠናቃለች።

እኔና ጥበቡ በቶሮንቶ የማውንት ሳይናይ ሆስፒታል ቆይታችን የመጀመሪያ ዙር ማብቂያ ላይ ነን: : እስካሁን ባለው የሕክምና ሂደት በጥበቡ አካል ውስጥ ብዙ ነገር አልፏል። የቆሽቱን መንዳት ተከትሎ በሆድ ዕቃው ውስጥ የሚጠራቀመውን ፈሳሽ ለማውጣት በሆዱ ለይ የተንጠላጠሉ የላስቲክ ከረጢቶች አሉ። ቀልጣፋ እግሮቹን ዛሬ እንደልቡ አያዛቸውም። የሚሰጠውን የሕመም ማስታገሻም ጥሶ አልፎ አልፎ የሚያስማው የጣዕር ድምፅ በእኔም ነፍስ ውስጥ እንደሰይፍ እያለፈ ነፍሴን እጥፍ ዘርጋ ያደርጋታል። ያ በጥንካሬውና በጉልበቱ ብርታት የሚታወቀው የኔ ጎበዝ ጥበቡ ኃይለሥላሴን ቀስስተኛ ሆኖ ማየት እኔ ልቋቋመው በማልችለው የኃዘን ማዕበል ውስጥ የሚወረውረኝ ነገር ነበር።

ነገር ግን፡- በጣዕር በሚያስማቸው ቃላት መካከል ትንሽ እፍታ ሲያገኝ ከእንደበቱ የማይለዩት የነፍሱና የመንፈሱ ድምፆች ውስጡን ፈልቅቀውት ይወጣሉ። "እግዚአብሔር ይክበር! . . . ኢየሱስ ጌታ ነው! . . . አምላኬ በዙፋኑ ላይ ነው! . . . ." ሲል ሲያናውጠን የመጣውን ነውጥ የመበታተናቸው ጉልበት አስደናቂና መለኮታዊ ነበሩ። እኔንም ደካማዋንና እርብትብቷን ባለቤቱን እንደሌላ ብርቱ ሰው አድርገው በጎኑ እንድቆም ኃይል ሆነውኝ ነበር።

አዎን! በሥጋው ጎስቋሉና ደክሞ ይታይ በነበረበት በሕመም አልጋው ላይ የጥበቡን በትዕግሥት፣ በፍቅር፣ በሰፊ ፈገግታና በብርሃን የተሞላ ፊት ዓይተው በወጡ ቁጥር፣ በገዛ መንፈሳቸው ተወቅሰውና ራሳቸውን መዝነው የወጡና ይህንንም የመሰከሩ ብዙዎች ነበሩ።

****

## ቀብሩ የት ነው?

ትገዝ ይለኛል በኦክቶበር ወር አንድ ሰኞ ጥበቡ ደጁ ናፍቆታል። ወጣ እያለ መመለስ ይችል እንደሁ 'የዴይ ፓስ' እንዲሰጠው ሐኪሞቹን ጠየቃቸውና ከድፍን ሁለት ወር በኋላ መጋቢ ዘካርያስ በመኪናው ይዘን ወጣ። ለመጀመሪያ ጊዜ ያን ከሞት ጋር ትንቅንቅ የገጠምንበትን ሆስፒታል ጥበቡን በሕይወት ይዘን መውጣታችን ልዩ ሲቃ ውስጥ መንፈሴን ጨምሮታል። ከተማውን ዞር ዞር ሊያደርገን ነበር አወጣጡ መጋቢ ዘካርያስ።

"እይ! በዚህ ወቅት መገኘት ያለብን ለምስጋና በእግዚአብሔር እግሮች ስር ነው፤ ቤተክርስቲያን ውስጥ!" አልኩ በውስጤ ነፍሴ እግዚአብሔርን እየባረከች። ድንገትም፣ መጋቢ ዘካርያስ አቅጣጫውን ቀየረና "እህት ሊሻን አሁን የምንሄደው ወደ ቤተክርስቲያን ነው! የሚገርምሽ

ሰኞ ሰኞ የቤተክርስቲያናችን ቁልፍ ፈጽሞ በእጄ ሆኖ አያውቅም። ዛሬ ግን ቁልፉ በእጄ ስላለ ወደዚያ ነው የምንሄደው!" አለኝ።

"የልቤን መሻት እንዴት አገኘኸው! ኦ ፓስተር ዘካርያስ እግዚአብሔር ይባርክህ፤! እሱን ነበር እኮ አሁን ልቤ እየተመኘ የነበረው፤" አልኩት። ነፍሴ በውስጤ ፈነጠዘች። እንደደረስን ከመኪናው ወርደን በቀጥታ ወደ መሰብሰቢያው አመራን። አዳራሹ ያኔ አገስት 19 ሌሊት ከመታመሙ በፊት ጥበቡ ያገለገለበት አዳራሽ ነው፤ መድረክ ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ ያስቀየረውን የሮሜ 8፡28ን መልእክት ያካፈለበት ቦታ። "በሕይወቴ ጣልቃ እየገባ… መንገዴን አቀና" እያለ ከልብ አምላኩን አምልኮ ያስመለከበት ስፍራ።

አሁን ሦስታችንም በእግዚአብሔር ፊት ሆነን እግዚአብሔርን "ተመስገን!" እያልነው ነው። ጥበቡ ሙሉ ለሙሉ በሆዱ ምንጣፉ ላይ ተኝቶ እግዚአብሔርን ያመሰግናል። ድንገት በምስጋናችን መኻል መጋቢ ዘካርያስ አዳራሹን ለቆ ሲወጣ አየሁት። የምስጋና ጊዜያችንን ጨርሰን ስንወጣ ጥበቡን ደግፈን ወደ መኪናው ከተመለስን በኋላ መጋቢ ዘካርያስ የነገረን ነገር ግን እጅግ አስገርሞናል።

"ከጸሎት መኻል ድንገት የወጣሁት የዶክተር ጥበቡን የኮምፒዩተር ሻንጣ መኪና ውስጥ ትተን ስለገባን ይዤው ልመጣና ተቻኩዬም መኪናዬን በትክክል ስላላቆምኳት ለማስተካከል ብዬ ነበር። ቤተክርስቲያኑ በር ላይ ያጋጠመኝ ሰው ግን ምንነቱና ማንነቱ በጣም አጠያያቂ ሆኖብኛል። ረዥምና እጅግ ዘመናዊ ሰው፣ በጣም ውድና ሥርዓቱን የጠበቀ ጥቁር ሱፍ ልብስ የለበሰ፣ ከራቫቱና ደረት ኪሱ ላይ ያደረገው መሃረብ ልዩ የሆነ፣ በላዩ ላይ ላባ የተሻጠበት ባርኔጣ ያደረገ አንድ ሰው ቆሞ አገኘሁ። ሰውዬውም፡- "የቀብሩ ሥነስርዓት እዚህ ነው?" ሲል ጎላ ባለ ድምፅ ጠየቀኝ። እኔም ጥያቄው አስገርሞኝ፡- "የቀብር ሥነስርዓት?! በሰኞ ቀን እዚህ ቤተክርስቲያን . . .?" ስል መልሼ ጥያቄውን በራሴ በጥያቄ መለስኩለት። ሰውዬው በተበሳጨ ድምፅና አነጋገር፡- "አዎን! እዚህ ነው አድራሻው!" ብሎ መለሰልኝ።

በሰውዬው ሁኔታ በጣም በመደነቅ፡- "አይ! ይቅርታ! የአድራሻ ስህተት ሊሆን ይችላል። በአካባቢው ሌሎች ቤተ-ጸሎቶች ስላሉ ወደ እነሱ ሄዶ መጠየቅ ይሻላል። እዚህ ግን የሚካሄድ የቀብር ሥነ-ስርዓት የለም!" አልኩት። ሰውዬው አሁንም በቁጣና በብስጭት እየተራመደ ከጊቢው ሊወጣ መንገዱን ሲጀምር በመገረም እንደተሞላሁ ወደ መኪናዬ አመራሁ። ቶሮንቶ ለብዙ ዓመታት ስኖር አንድም ቀን እንኳ በየትኛውም ቤተክርስቲያን የቀብር ሥርዓት በሰኞ ቀን ሲካሄድ ዓይቼም - ሰምቼም አላውቅም፤ ቅዳሜ እንጂ። ተለይቼው መሄድ እንደ ጀመርኩ ይሄን ቁጡና ብስጩ የሆነ ሰውዬ ላየው ዞር አልኩ። መሬት ይግባ ሰማይ የት እንደሄደ አጣሁት።

ድንቅ ነው! አምላካችን እግዚአብሔር በጥበቡና በሞት መካከል እንዴት ጣልቃ እንደገባ! በእርግጥ የጠላታችን የዲያቢሎስ ሐሳብ በዚያች በመንፈስ ሆኖ ባገለገለባት ቤተክርስቲያን የጥበቡን የቀብር ሥነ-ስርዓት ሊያካሂድ ነበር ማለት ነው።

ክፉ ምክሩን የበተነ፣ ወጥመዱን ሁሉ የሰባበረበት አምላካችን ለዘላለም የተመሰገነ ይሁን! እኔና ጥበቡ በገጠመን በዚህኛው የሕይወት ሠልፍ ሁሉ እግዚአብሔር ለኛ ተሠልፎ እስከዚያች ዕለት እንኳ ነጥብ በነጥብ ሰይጣንን እንዴት ድል እንደነሳልን በዓይነ ሕሊናዬ እንደፈልም ያልፍ ጀመር።

"ምድረበዳ" ብሎ ሰይጣን ባሰበው ስፍራ፣እግዚአብሔር እኔንና ጥበቡን በፍቅር ሊያገለግል

በቆረጠ ሕዝብ አጠረን። በግለሰብ ትከሻ የማይቻለውን በሚሊዮን ዶላር በሚቆጠር ወጪ የባሪያውን መኝታ አነጠፈለት። በታወቁ የሕክምና ባለሞያዎች በክብርና በሞገስ ተንከባከበው። የፍቅራችንና የትዳራችን አምላክ ባጠገቡ ሆኜ "አይዞህ! የኔ ፍቅር እኔ አለሁ" እንድለው አደረገ። በዚህ በጭንቁና በመከራው ሰዓት በአምላኬ እርዳታ እጆቹን ይዤ እንድደግፈው፣ ምንጊዜም ካጠገቡ መለየት የማልፈልገውን 'በኀዘን ቢሆን በደስታ' ብዬ ቃል ለገባሁለት ውዴ... በዚያ እንድገኝ . . አደረገ።

- በወገኖቼ የኑሮ ውጥረት ላይ ተጨማሪ ሸክም ሆንኩኝ ብዬ እንዳልሳቀቅ...ለሴት ባሪያው የውሎ አበል በዶላር እየተከፈለኝ ባማረና ምቹ በሆነ ትልቅ ሆቴል ባሪያውን እንዳስታምመው አስቻለኝ።
- ሁልጊዜ ከሁለት ሰው ሙሉ ቁርስ ጋር ጽዳቱና እቃ አጠባው እንኳ ሳይቀር በሆቴሉ ሠራተኞች እንዲከናወን ተደረገ።
- ልጆቻችንንም ሆነ ከአሜሪካና ከሌላ ሰፍራ የሚመጡ እንግዶቻችንን፣ የማስተናግድበት ሳሎንና መኝታ ቤት፣ ዘመናዊ ኪችንና የራሱ ባኞ ቤት ያለው ስፍራ አዘጋጀልኝ።
- ከረምትና በጋ በተፈራረቀበት የስድስት ወራት ቆይታዬ የሆስፒታሉ ርቀት በኔ የቀስታ እርምጃ ስምንት ደቂቃ ብቻ ነበር። ከአካባቢው ጸጥታ የተነሳ በሌሊት ሆነ በቀን በፈለግሁት ሰዓት ብቻዬን ብሆንም የማያስፈራ ቦታ ነበር።

****

*ሌላ ትድግና*

> "ይሽሩን ሆይ! በሰማያት ላይ ለረድኤትህ በደመናትም ላይ በታላቅነት እንደሚሄድ እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም። መኖሪያህ የዘላለም አምላክ ነው፣ የዘላለምም ክንዶች ከአንተ በታች ናቸው፣ ጠላትህን ከፊትህ አውጥቶ አጥፋው ይላል። እስራኤል ተማምኖ የያዕቆብም ምንጭ ብቻውን እህልና የወይን ጠጅ ባለበት ምድር ይኖራል፣ ሰማያቱም ጠልን ያንጠባጥባሉ። እስራኤል ሆይ ምስጉን ነህ፣ በእግዚአብሔር የዳነ ሕዝብ እንደ አንተ ማን ነው? እርሱ የረድኤትህ ጋሻ የከፍተኛነትህም ሰይፍ ነው። ጠላቶችህም ይገዙልሃል አንተም ከፍታቸውን ትረግጣለህ።" (ዘዳ 33፡26-29)

ሁለት ወር ከአንድ ሳምንት ሲያከመው የሰነበተው የሐኪሞች ቡድን የጥበቡ የጤንነት ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ የተሻለው ባይሆንም በቀጠሮዎች እየተመላለሰ ሕክምናውን እስከ ጊዜው እንዲቀጥል ወሰነ። ኦክቶበር 23 ከማውንት ሳይናይ ሆስፒታል ወጣንና እኔ ወደ ምኖርበት ሆቴል ይዘነው ገባን። እግዚአብሔርን አመስገንነው፤ ጥበቡም ለመጀመሪያ ጊዜ ያረፍኩበትን ሆቴል ዓይቶ ስለእግዚአብሔር ቸርነት ደስ አለው።

ከሆስፒታሉ ውጭ ሆቴላችን በሳለፍነው ጊዜም ከወገኖች ጋር ስንጸልይ እግዚአብሔር በመካከላችን ሲገኝ ዓይተነዋል። ከነዚህ ባንዱ ቀን እግዚአብሔር በፓስተር ዘከርያስ ውስጥ በመጣ መልእክት፣ ስለጥበቡ ሲናገር "ገና ለክብር ይፈለጋል" ያለን ጊዜም ትዝ ይለኛል። ሆቴል በነበረን ቆይታችን ኖቬምበር 18 ጥበቡ በታመመ በሶስተኛው ወርና ከሌሊቱ ልክ በዚያኑ ሰዓት ያየነውን አንድ የእግዚአብሔር ትድግናም አልረሳውም። ያን ዕለት ጥበቡ ፓስተር ዘከርያስን አግባብቶት (አብረኸን ካላደርክ ብሎ) ሆቴላችን አሳድሮታል።

እናም ፓስተር ዘካርያስ አብሮን ባደረበት በዚህ ሌሊት ነው ከሌሊቱ ልክ 9 ሰዓት። ጥበቡ ካጠገቤ ተነስቶ ወደ መታጠቢያ ቤት ሲሄድ ዓይኼው ደርሶ እስኪመለስ በንቃት አዳምጠዋለሁ። ድንገትም ድው! የሚል ድምፅ ሰማሁ። ለካስ ፓስተር ዘካርያስም እንደኔው ነቅቶ ይጠባበቅ ኖሯል። ተራሩጠን ወደ መታጠቢያ ክፍል ስንገባ ጥበቡን ወለሉ ላይ አዙሮት ወድቆ አገኘነው። ጭንቅላቱ ከዕብነበረድ ድንጋዩ ጠርዝ ያመለጠው ለጥቂት ነበር፤ አግኝቶት ቢሆን እንዴት ዘግናኝ አደጋ በደረሰበት ነበር። የመላእክቱን ጥበቃ በዙሪያው አድርጎ ዓይተናልና ድንጋጤያችንን ወደ ልዩ ምስጋና እግዚአብሔር ለወጠልን። ይህም የአምላካችንን ሌላ ትድግናውን ያየንበት ቀን ሆነልን። ከሆስፒታሉ ውጪ ወር ያህል እንኳ ሳንቆይ እንደገና ለተጨማሪ ሕክምና መግባት ነበረብን። የእምነት ትግላችንም በእግዚአብሔር ሕዝብ የፍቅር ርብርቦሽ ቀጠለ።

መቼም ፓስተር ዘካርያስ ለጥበቡ በጣም የሚመቸው ሰው ስለነበረ ምንጊዜም ባይለየው ይወዳል። ሆስፒታል ሳለን ጥበቡ የሚፈልገውን ወይም የሚያስኘውን ነገር፣ ፓስተር የትም ገብቶ የጥበቡን ምኞት ማሳካት ደስታው ነው። ከብዙዎቹ አንድ ሁለቱን ላንሳላችሁ።

ከሚደረጉለት የተለያዩ የሕክምና ክትትሎች መልስ ጥበቡ በጣም ስለሚበርደው በኤሌክትሪክ የሚሞቅ ብርድልብስ እንድናደርግለት ይፈልጋል። በጊዜው ያን ማግኘት ችግርና ብርቅ ነበር። ፓስተር ዘካርያስ ግን የትም የትም ብሎ ይዞ ከተፍ ይላል።

በሌላ ጊዜ ደግሞ ጥበቡ ከተኛበት 14ኛ ፎቅ ላይ ከሚገኘው ክፍሉ ወደ 1ኛው ፎቅ መውረድና ሻይ ቡና እያሉ የኔን መምጣት እንዲጠባበቁ ለወንድም ዘካርያስ አሳብ ያቀርብለታል። "እሺ ዶ/ር ምን ችግር አለ! ቆይ ዊል ቼር አምጥተው እንዲረዱን የጤና ረዳቶች እንጥራ" ይለዋል።

መጥሪያ የተደረገላቸው ረዳቶች የውሃ ሽታ ሆነው ሲቀሩ፣ ፓስተር ዊልቼር ፍለጋ ቢወጣ ምንም ሊያገኝ አልቻለም። በዩኖቹን ወዲያና ወዲህ ሲያማትር አንድ አልጋ የሚያክል ተሽከርካሪ ትልቅ ወንበር ያገኛል (ይሄን ትልቅ ወንበር ሆስፒታል ውስጥ የሚጠቀሙት በሽተኞች አልጋ ሲሰለቻቸው እዚያ ላይ እግሮቻቸውን ወደላይ ከፍ አድርገውላቸው እንዲቀመጡ የሚያደርጉበት ነው)። ወንድም ዘካርያስ የጥበቡን ፍላጎትና ምኞቱን እንዳይፈጽምለት የሚያግደው ችግር የለም! በጥበቡ ላይ ደግሞ ተሰክክተው በደም ሥሩ መድሃኒቶችና ምግብ የሚያቀብሉትን ልዩ ልዩ ክረጢቶች የተሸከመ አንድ ተሽከርካሪ ብረት አለ። ያም ለፓስተር ችግር አልነበረም! ጥበቡን በጥንቃቄ ከአልጋው አውርዶ እዚያ ትልቅ ተሽከርካሪ ወንበር ላይ አስቀምጦ እነዚያን ሁለት ትልልቅ ተሽከርካሪዎች በአንድ አቀናጅቶ ይዞት ከዚያ ክፍል ወጣ። ወደታች ለመውረድም ሆነ ወደላይ ለመውጣት ሊፍቱ (አሳንሰሩ) ላይ የገጠማቸውንም ችግር በሁለቱ ምክክር አልፈውት፣ የጥበቡን ምኞት ፓስተር ፈጽሞለት ሲመለሱ መንገድ ላይ ተገናኘን። ደነገጥኩ። እነሱ ግን ባደረጉት ነገር ረክተውና ተደስተውም በሳቅ ሲፈነድቁ ስላገኘኋቸው ድንጋጤዬ ቀርቶ ውስጤን ፈንቅሎ በወጣ ሳቅ ተሞላሁ።

ልጆቻችንና የልጅ ልጆቻችን በየአጋጣሚው ወደ ቶሮንቶ መጥተው ከእኛ ጋር አሳልፈዋል። ታንክስጊቪንግ (የምስጋና ቀን)፣ የክርስቶስ ልደትና የፈረንጆቹ አዲስ ዓመት ለእኛ አምላካችንን የምናመሰግንበትና የምንሰባሰብበት ምክንያት ፈጥረውልናል። ጥበቡ ድሮም ቢሆን በጸሎትና በአምልኮ ብቻ ሳይሆን የወገኖች ሕብረትና ማዕድ አብሮ መቁረስ የሚያስደስተው ሰው ነው። በትዳራችን ዘመን ሁሉ በኖርንባቸው የተለያዩ አገራት በምንቀበላቸውና በምናስተናግዳቸው የእንግዶች ብዛት "የኢትዮጵያ ኤምባሲ" የሚል ስምም ያወጡልን ሰዎች ነበሩ። ባንድ ጊዜ ከሰላሳ ሰው በላይ ሊያስተናግድ የሚችል እንጀራና ወጥ ከቤታችን አይጠፋም! ለተለያየ መንፈሳዊ ስብሰባ

ወደምንኖርበት ከተማ መምጣታቸውን ከሰማን እንደጥንቱ የእምነት አባታችን እንደ አብርሃም ከቤታችን ጣሪያ ስር ገብተው ማዕድ እንዲቆርሱ ግድ ማለት የጥበቡ ልማድ ነው። እኔም ይህን መሳይ ንጹሕና ለበጣ የሌለበትን ጥበቡ ለሰዎች ያለውን ፍቅር ማገልገል፣ ደስታውንም ማየት ደስታዬ ነው። ለራሱ ከሚኀርስ ይልቅ ሌሎችን ማጉረስ የሚወደው ጥበቡ ዛሬ ግን ያለው በቤቱ ሳይሆን ሆስፒታል ውስጥ ነው። ሊጠይቁት የሚመጡትን ወገኖች በአልጋው ዙሪያም ቢሆን ሲበሉ ማየት ደስታው ነው። ይህ መሻቱ እንኳ እንዳይቀርበት እግዚአብሔር ያደረገልን ቸርነት ብዙ ነው።

በልደት በዓል ሰሞን ልጆቻችንና እህት ወንድሞቻችንም ከአሜሪካ እኛን ለመጠየቅ ተሰባስበው ነበር። ጥበቡ በልቡ ለእነዚህ ሁሉ የሚበቃ ምግብ በጥሩ ሁኔታ የሚያዘጋጅለት ሰው ገንዘብ ከፍለን እንኳን ባገኝ በማለት ሳይመኝ አልቀረም። የቶሮንቶ ወገኖች ግን ተመካክረው በልቡ ከተመኘውና ካሰበው በላይ ትልቅ ዝግጅት አዘጋጅተው ኖሯል። የሆስፒታሉን ኃላፊዎች አስፈቅደው ለገና ዴኮሬሽን ወደአስጌጡት አንድ ሰፊ ክፍል የጥበቡን አልጋ ወሰዱ። የምግብ፤ የኬክና የብስኩታ ብስኩት ዐይነቶች የሞሉበት ትልቅ የቡፌ ጠረጴዛ ተዘረጋ። በልቡ ተመኝቶ የነበረውን ሁሉ እግዚአብሔር አድርጎት በማየቱ የተሰማውን ትልቅ ደስታ ከእንባ ጋር መሰከረ።

ከወጣትነት ዘመናችን እስከዛሬ በመከራ ቢሆን በደስታ በእግዚአብሔር ቤት አብረን ብዙ ከተጓዝናቸው የቅርብ ጓደኞቻችንና ሚዜዎቻችን (የረቡዕ ሕብረት) ውድነሽ አዘነና ባለቤቷ ግርማ በጋሻው ናቸው። ኤድመንተን ካናዳ ልጃቸውን ለመዳር መጥተው ነበር። ውድዬ ለአንድ ሳምንት ያህል አብራን ለመሆንና ለመጸለይ ቶሮንቶ መጥታለች። ያን የምታውቀውንና የምትወደውን የእምነት አርበኛ ዛሬ ደክሞትና አሞት ማየቷ ትልቅ የልብ ሰብራት ቢሆንባትም የመጣችው ‘ አይዟችሁ ! ’ ለማለት ስለሆነ እንባችንን ዋጥ፣ ወገባችንን ጠበቅ ለማድረግ ተስማማን። እኛን በዚያ ሁኔታ ዓይታን እንደመንገደኛ ለመሄድ የፍቅር ልቧ ስላልፈቀደላት የአንድ ሳምንት እቅዷን ወደ አንድ ወር ለወጠችው።

እግዚአብሔርም በቶሮንቶ ያደረገልንን ቸርነትና እንክብካቤ ራሶቻችንን በዘይት የቀባልንን፣ የሆነልንንም ሞገስና ክብር ዓይታ አምላካችንንና አምላኳን አመስግናለች። ታዲያ አብረን እየዋልን እያደርን ባሳለፍነው የአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አንድ ፈልጋና አምሯት የቆየ ነገር ኖሯል። በወገኖች አስደናቂ ፍቅር ከሚዘረጋልን ማዕድ መሐል ፈልጋ ያጣችው፣ ሽሮ ነበር። ቢቸግራት የትንሹም የትልቁም ጉዳያችን በላቤት ለሆነው ለእግዚአብሔርም ነግራው ኖሯል። እናም እኔና ውድዬ ምሳ ሰዓት አካባቢ ሆስፒታል ውስጥ ከጥበቡ ጋር ሳለን ድንገት አንዲት እህት ከሚያስገርም የምግብ ዝግጅት ጋር ገባች። የወጡ፣ ያታክልቱ፣ የጥብሳጥብሱ ባይነት ባይነቱ ወጥቶ ተሰለፈ፤ በምታምር የሸክላ ድስት ሽክን ብላ ከተሠራች ተበልታ ከማትጠገብ ሽሮ ጋራ።

በሆስፒታሉ የማዕድ አገልግሎት ዙሪያ የማልረሳት እህት፣ ካጠገባችን ባለመለየት በፍቅር በጸሎትና በመስጠት ከገለገሉን ቅዱሳን መሐል አንዷ ኢንጂነር አስታረቀች ሻኛ ነበረች። ቀን ሥራዋ ላይ የደከመችው ሳያንሳት እኛን ማገልገል ደግሞ ደስታዋ የሆነ። አስታ ዘወትር በየማታው የራት ሰዓት ላይ ሆስፒታሉ ፍሪጅ ውስጥ ያስቀመጥነውንም ሆነ አዲስ የመጣውን ምግብ መልክ መልክ ትስጠዋለች። በያይነቱና በየሳህኑ አደላድላ በምሽቱ ለተገኘነው ሁሉ ታድላለች። እግዚአብሔር ይባርክሽ አስታ !

****

*እኔና ሐኪሞቹ!*

ቶሮንቶ ማውንት ሳይናይ ሆስፒታል ውስጥ እያለን በጋውን የሚተካው የከባድ ክረምታቸው ጊዜ ገባ። ክረምቱ የመጣው ግን በጥበቡ ሕይወት ላይ እንደገና የአደጋ ቈጋግ ካጠላበት ሁኔታና ጊዜ ጋር ገጥሞ ነው። ቀደም ሲል ካንዴም ሁለት ሶስቴ ሐኪሞች በተለያየ ጊዜ ውስጡ አየን የሚሉትን "አየር" ፍለጋ ኦፕራስዮን ሊያደርጉት የቃጡትን መቃጣት በእግዚአብሔር ፊት እየወደቅንና እሱም ጣልቃ እየገባልን አስጥሎልናል። ዲሴምበር 3 ምሽት ላይ ግን ሕመሙ ካለፉት ጊዜያት ለየትና ጠንከር እያለ ስለመጣ ሐኪሞቹ ተጠርተው ባደረጉት ምርመራ በአሥር ደቂቃ ውስጥ ኦፕራስዮን መደረግ እንደሚኖርበት ወሰኑ። ሁኔታው ከባድና አስቸኳይም ስለነበር ለእግዚአብሔር በጸሎት አሳልፈን ሰጠነው። ዐይኖቹ በእንባ ቈጋግ ተሸፈነው በጥድፊያ እየተሯሯጡ ይዘውት ሲበሩ ሳያቸው እንደገና በሕያዋን ምድር የኔን ውድ ጥበቡ የማየው አይመስልም ነበር።

> "ግን እግዚአብሔር ሆይ ገና 'ለክብር ይፈለጋል' ብለኸን አልነበር? ስለዚህ እግዚአብሔር ሆይ ጉልበትህን ተማምነህ ይህን ተናግረሃልና ባሪያህን ዐይን ለዐይን እንድንተያይ ታደርጋለህ" አልኩኝ በዕንባ።

እናም በዚያች በማልረሳት ምሽት አብረውኝ ከነበሩት ጋር ሞትን ልንናጠቅ በእግዚአብሔር ፊት ቆምን! ለልጆቻችን ደወልኩ በሚቀጥለውና በሚያገኙት አውሮፕላን ወደ ካናዳ እንዲመጡ። በጸሎት የትግል ሜዳ አብረውን እንዲቀላቀሉ ወደያሉበት ለቅዱሳን ደወልን።

ስድስት ሰዓት ይፈጃል ተብሎ የተነገረንን ጊዜ በሁለት ሰዓት ብቻ አሳጥሮልን ጥበቡን በሕይወት ከዚያ አስጊ ኦፕራሲዮን አወጣልን። ግን ውጤት አልባ የሆነ ቀዶ-ጥገና ነበር፤ እግዚአብሔር የጥበቡን ሕይወት ጠበቀልን እንጂ። ሐኪሞቹ ሆዱን ከፍተው የጠረጠሩትን የችግር (የአየር) ምንጭ ሊያገኙት አልቻሉም። ስለዚህም መልሰው ዘግተውታል።



ጥበቡ ከአይሲዩ በወጣ በአራተኛ ቀኑ 60ኛ ዓመቱን ስናከብርለት

ከባድ የሞት ጥላ ያጠላባቸው ቀናት በአይሲዩ እንደገና አሳለፍን! ሰይጣን የጥበቡን ስቃይና ጣር ለመጨመር ተደጋጋሚ ሙከራ አድርጓል። ሐኪሞችን እንኳ እያዘናጋ በሚችለው ቀዳዳ ሁሉ ሊያጠቃው ሞክሯል፤ ጥበቡ ሊደረግለት ስለሚገባው ሕክምና በጥንቃቄና በንቃት እንድከታተል፣ ካስፈለገም እንድከራከርና ስሕተቶች እንዲታረሙ የእኔን አእምሮ በመክፈት አምላኬ ሲጠቀም ዓይቼ አክብሬዋለሁ።

ስለዚህም ተመልካች እንደሌለው ሰው በእጃቸው የተገኘ አለመሆኑ ገብቷቸው ሁሉን በጥንቃቄ እንዲያደርጉ ሆኗል። ተጣድፈው አደገኛ ውሳኔዎች እንዳይወስኑ፣ እስኪገባኝ እንዲያስረዱኝ፣ ካልመሰለኝና የሚሉት ካላረካኝ በይደር ቆይቶ ኦፕራስዮንን ያህል ነገር አላስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙትና ሲቀር ዓይቻለሁ። ሊሰጡት ስለሚገባ የመድኃኒት ዓይነት ከሐኪሞች ጋር ተከራክሬ አሸንፌያለሁ።

ቀዶ ጥገናውን ያደረጉለት ሐኪሞች የሚያዩት የተወሰነ ቦታ ሆዱን ገለጥ እያደረጉ ነው። እኔ ግን የውዴን የጥበቡን ሁኔታ የማውቀው ከራስ ጸጉሩ እስከእግር ጥፍሩ፣ በመንፈሱም በውስጡ እንኳ ይሰማው ይሆናል ብዬ የማስበውን ስፍራ ሁሉ ጭምር ነው። እናም ከሐኪሞቹ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ሌሎች ሌሎችም የመድኃኒት ዐይነቶች ሰዓታቸው እየተጠበቀ በየተራ ከደም ሥሩ ጋር ባገናኙት መስመር ይተላለፋል። ለሰውነቱም አስፈላጊ የሆነ ግሉኮስም (ኢንፊዩገርን) እንዲሁ። ከሁለት ቀናት በኋላ ሁኔታውን በንቃት በምጠባበቀው በዐይኖቼ ፊት ጥበቡ ወደ ውስጡ ያለማቋረጥ በሚጨመረው ፈሳሽ ምክንያት ሰውነቱ ያለመጠን እየጨመረ መጣ። ስለዚህ ጉዳይ ያስጨነቀኝንና ሊቃለልለት ያስፈልጋል ብዬ ያሰብኩትን ችግር ተረኛውን ሐኪም ማናገር ስለምፈልግ ጥሩልኝ ስል ነርሶቹን ጠየቅሁ።

ደጋግሜ ባስጠራትም 'ቢዚ' ነኝ እያለች ተረኛዋ የአይሲዩ ሐኪም አልመጣ ብትል፣ "አሁን መጥተሽ ካላናገርሺኝ ከዚህ ስፍራ አልነቃነቅም ማደር ቢያስፈልግም አድራለሁ"፤ በሚለው ቁርጠኛ መልእክቴ ምክንያት መጣች። ሰውነቱን ገልጬ፣ "እስከዚህ ድረስ እስኪጨምር ምንድነው የምትጠብቁት?" ብዬ አሳየኋት። ቀጥሎም፡- "ለምንስ ቢያንስ የገባውን ፈሳሽ ከሰውነቱ በተመጣጣኝ ደረጃ በሽንት እንዲወጣለት 'ሌሲክስ' (Lasix or Furosemide) አይሰጠውም? ... ምን እስኪሆን ነው የሚጠበቀው?" ብዬ ስጠይቃት ደንገጥ ብላ፡- (መድሃኒቱን ስሙን ልጠቅስላት በመቻሌ፣) "አይ! ይሄን መድኃኒት አሁን እኔ ላዝለት አልችልም፤ እሱን የሚያክሙት ሐኪሞች ናቸው እንጂ፤ አሁን ደግሞ እርብ ማታ ነው መሽቷል፤ እሁድና ቅዳሜም እነሱ አይገቡም!" ስትለኝ ጭራሹኑ ውስጤ ተቆጣ! ጠንከር ባለ ድምጽም፡-

> "ይቅርታ ዶክተር፣ ይሄን መልስ ካንቺ አልጠብቅም! እዚህ የተመደብሺው የሕመምተኞችን ስቃይ ለማስታገስና ካንቺ በላይ የሆነ ነገር ከገጠመሽም ከሚመለከታቸው ጋር ተመካክረሽ ልትወስኚ መስሎኝ! ሰኞን መጠበቅ የማይችለውን የእርብ በሽተኛ ምንም ልታደርጉለት ካልቻላችሁ በጣም አዝናለሁ! ያም ሆነ ይህ ባለቤቴ ላይ ለማየው ችግር መፍትሄ ካላገኘሁ የሚመለከታቸውን ሐኪሞች ባስቸኳይ እንድትጠሪልኝ እፈልጋለሁ!"

የብሶቴንና በውስጤ በሰሞኑ የተጠራቀመውን (የሆነው) ሁሉ እየተናነቀኝ ተናገርኳት! በዚሁ መንፈስ ወጥቼ አይሲዩ ቤተሰብ መቀበያ አዳራሽ ወዳሉት ወገኖች ሄጄ የሆነውን ነግሬያቸው ጸሎት ገባን። በዚህ መሐል ትልቋ ልጃችን እምነት አባቷ አጠገብ ልትሆንለት ገብታ ነበር። ያቺ የሞገትኳት ሐኪም ልጄን እምነትን፣

> *"Tell your mom she has won the battle, the doctors have decided to give your dad the Lasix"* "ጦርነቱን እንዳሸነፈች ለእናትሽ ንገሪያት፤ የጠየቀችው ሌሲክስ ለአባትሽ እንዲሰጠው ሐኪሞቹ ወስነዋል!" ተደነቅኩ።

በሐኪሞቹ ሊሰተዋል የተገባው ነገር ከነሱ እምልጦ ከእኔ የመነጨበት አጋጣሚ ብዙ ነበር። ከዚህም የተነሳ የካናዳዎቹ ሐኪሞች በተለያየ ጊዜ "ባለቤትህ 'ጂንየስ ናት' ... 'ስማርት ናት' 'የሰጠችን አሳብ ጠቅሞናል' እያሉ በተለያየ ጊዜ ለጥበቡ ሲነግሩት ተሰምተዋል።

****

## "ገና ለክብር ይፈለጋል!?"

አሁን የቶሮንቶ ወገኖች ፍቅር እየገተተኝ እንጂ ካናዳን ለቀን መውጣት እንዳለብን ይሰማኝ ጀመር። ይሄ ስሜት የኔ ብቻ ሳይሆን የልጆቼም ጭምር ስለሆነ የጥበቡ መሥሪያ ቤት እንዲያውቀው አደረግን። የእስካሁኑ የካናዳ ሕክምና ይብቃና የአሜሪካው ደግሞ ይሞከርልን በሚል። ዩኒሴፍም ጉዳዩን በትጋት ይከታተል ነበርና ጥበቡ ባስቸኳይ ወደ አሜሪካ ለተጨማሪ ሕክምና የሚወሰድበትን ዕቅድ አወጣ። ጥቂት እንቅፋቶች ግን በፊታችን ተደቀኑ።

- እስካሁን ካናዳ የታከመበት የተባበሩት መንግሥታት ኢንሹራንስ (ቫንብሬዳ የሚባል) የሚያገለግለው ከአሜሪካ ውጪ ላሉ የተባበሩት መንግሥታት ሠራተኞች እንጂ አሜሪካ ውስጥ አለመሆኑ፤
- እኛ ደግሞ የወቅቱ የሥራ ምድባችን እስራኤል እንጂ አሜሪካ ውስጥ አለመሆኑ፤
- ኢንሹራንሱ ሊሠራና የማይተናነስ ሕክምና ሊያገኝ ይችላል ተብሎ ወደ ሚታሰብበትና ወደ ምድብ የሥራ ቦታችን ወደ እስራኤል እኛን ለመላክ የጥበቡ ሁኔታ የረዥሙን ሰዓት በረራ ሊቋቋመው አለመቻሉ፤
- የአሜሪካው "ኤትና" የተባለው ሌላ ኢንሹራንስ ጥበቡን እንዲያገለግለው ለማድረግ ጥበቡ የአሜሪካ ነዋሪ ወይንም አሜሪካ ውስጥ የተመደበ የተባበሩት መንግሥታት ሠራተኛ አለመሆኑ፤

እነዚህን የመሳሰሉ እንቅፋቶች ጥበቡን ይዘን ወደ አሜሪካ እንዳንጓዝ ስለተደቀኑ ጥቂት ቀናት በጸሎት እንደቆየን ከመሥሪያ ቤቱ ተደወለልኝ።

"ለገጠመን ችግር መፍትሄ አግኝተናል፤ በሚገርም ሁኔታ! እንዳጋጣሚ ጊዜው አሁን ጃንዋሪ፣ የተባበሩት መንግሥታት ሠራተኞች ከነበራቸው ኢንሹራንስ ወደሌላ መለወጥ ቢፈልጉ መብታቸው የሚጠበቅበት ጊዜ ላይ ነን። ይህ በዓመት አንዴ የሚሰጥ ዕድል ነው። በተጨማሪ ደግሞ ምንም እንኳ እናንተ ምድባችሁ እስራኤል ቢሆንም፤ ልጃችሁ ትደነቅ አሜሪካ ውስጥ ሕጋዊ ተማሪ ስለሆነች የዚህ የአሜሪካው ኢንሹራንስ ተጠቃሚ የመሆን መብት አላት። እናንተ ደግሞ በልጃችሁ ምክንያት የነበራችሁን ቀይራችሁ የአሜሪካው ኢንሹራንስ ተጠቃሚዎች የመሆን ሕጋዊ መብት አላችሁ፤" ነበር የስልኩ ፍሬ ሐሳብ።

ይደንቃል! 'አጋጣሚ' ይሉታል ሰዎች! እኛ ግን የጊዜ ሁሉ ባለቤትና ተቆጣጣሪ የሆነው አምላካችን የካናዳው ነገራችን በድል የሚጠናቀቅበት ትክክለኛ ሰዓት ላይ እንዳደረሰን አወቅን። በወጀብና በዓውሎ ነፋስ ውስጥ መንገድ ባለው አምላካችን ፊት እነዚያን ትልልቅ እንቅፋቶች ሁሉ የክብሩ መገለጫ መረማመጃዎቹ አደረገና የአሜሪካውን መንገድ ወለል አድርጎ ከፈተው። እናም ውሳኔያችንን ለቶሮንቶ ማውንት ሳይናይ ሆስፒታል ሐኪሞች ስንነግራቸው ተደናገጡ። "ቅር የተሰኛችሁበትና የምናሻሽለው ጉዳይ ካለ ንገሩን" እንባል ጀመር።

ይህ ይሆናል ብለው አልገመቱም፤ ምናልባትም ከመሻል ይልቅ በእጃቸው እያሽቆለቆለ የመጣው የጥበቡ ጉዳይ በምድረ ካናዳ በሞት ይደመደማል የሚልም ግምት ነበራቸው። ልባችን ከዚያ ሆስፒታል ከወጣ ቆይቷልና የምናደርገው የሐሳብ ለውጥ አልነበረም። ልጆቻችን በሚኖሩባት በዴንቨር ኮሎራዶ ስመጥር ሐኪሞች የሚገኙበት ሆስፒታል ልጆቻችን ሲፈልጉ፣ "ዩኒቨርሲቲ ኦፍ ኮሎራዶ ሆስፒታል" ትክክለኛው ምርጫ መሆኑን አረጋገጡ።

ይህ ሆስፒታል በአዳዲስና ዘመናዊ መሣሪያዎች ተሟልቶ ከመሐል ከተማ ወደ ሰፊና አመቺ ቦታ ተዛውሮ በቅርቡ ሥራውን ጀምሯል። ሆስፒታሉ በማናቸውም ረገድ የተሟላ ኃላፊነት ከወሰደው ዩኒሴፍና አዲሱ ኢንሹራንስ "ኤትና" ጋር ተፈራርሞ ከባድ ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ የተባበሩት መንግሥታትን ዲፕሎማት ጥበቡ ኃይለሥላሴን በደስታ ሊቀበለው ዝግጅት አደረገ። የሁኔታዎች እንዲህ ሰምሮ መገጣጠም "ገና ለክብር ይፈለጋል" የሚለውን መልእክት ትዝ አሰኘኝ። የኔን ውድ ባሪያውን ጌታ እግዚአብሔር እንዴት እንዳከበረው አስተዋልሁ።

ቶሮንቶ ለዴንቨር አስፈላጊውን ዶክዩመንት አስረከበ። እኔንና ጥበቡን ብቻ ከሁለት ነርሶችና ፓይለቶች ጋር ይዞን የሚበር አውሮፕላን የተባበሩት መንግሥታት አዘጋጀ። ስድስት ወራት በፍቅር፣ በፍጹም መስጠትና መስዋዕትነት አብረውን የተጋደሉልንን ወገኖቻችንን ተሰናብተን የቶሮንቶን አየር ለመልቀቅ በረራ ጀመርን። ጥቂት እንደተጓዝን ግን ከፓይለቶቹ ዘንድ አንድ ያልተጠበቀ አሳሳቢ ጉዳይ ተነገረን።አውሮፕላኑ የአየር ፕሬዠር ችግር ስለገጠመው ቴክኒሽያኖች እንዲያስተካክሉት ወደ ቶሮንቶ በመመለስ ላይ ነን!" በምድረ ካናዳ ቢቻለው በሞት የኛን ነገር ሊደመድም ሰይጣን ያደረገው የመጨረሻ የሞት የሽረት ትግል!

እናም ይሄን የጠላቴን ተግዳሮት ሰረዳ ቋንቋ ጠፋብኝ። ከመንፈስ ቅዱስ ስለተሰጠን በልሳን የመጸለይ ስጦታ እግዚአብሔርን ያመሰገንኩበት አንዱ ያ ቀን ነበር። የጠላት የዲያብሎስን ሥራ ባየርና በምድር የሚሰሩትን የጨለማ ሠራዊት በእግዚአብሔር ስም እያሰርኩ ቶሮንቶ አየር ማረፊያው በሰላም ደረስን። የተባሉት ቴክኒሽያኖች ያን አውሮፕላን ሊሰሩት አልቻሉም ችግሩ ጠንከር ያለ ነበርና። ስለዚህ ሌላና ልዩ እንዲያውም ከፊተኛው ያማረና የተሻለ ምቾት ያለው አውሮፕላን ቀርቦልን አምላካችን በክብርና በደህና አሜሪካ አደረሰን። አምቡላንስ አውሮፕላን ማረፊያው ተዘጋጅቶ ይጠብቀን ነበርና ለጥበቡ የተዘጋጀለትን መኝታ ለመያዝ ወደ ሆስፒታሉ አመራን። ከልጆቻችንና ዴንቨር ከተማ ይጠብቁን ከነበሩት ወገኖቻችን ጋር በድል ፌብሩዋሪ 15 ቀን 2008 እ.ኤ.አ ተቀላቀልን።

በአሜሪካ የሐኪሞቹ አቀባበል የነርሶቹና የጤና ረዳቶቹ መንፈስ፣ ፈገግታቸውና ሥርዓታቸው ከካናዳዎቹ በጣም የተለየና ደስ የሚያሰኝ ነበር። በቶሮንቶውና በዴንቨሩ ያየር ንብረት መካከል ያለው ልዩነት ሁሉ እንኳ ሳይቀር ከጨለማ ወደ ብርሃን የመውጣት ያህል ነበር! ካናዳም ሆነ አሜሪካ ወቅቱ በሁለቱም አገሮች የክረምትና የበረዶ ጊዜ ነበር። ልዩነቱ ግን ቶሮንቶ እንደ ግድግዳ ተከምሮ በነበረው የበረዶ ክምር ላይ ባብዛኛው የሚውለው የጨገገው ቀን ሲሆን፣ ዴንቨር በሚጥለው በረዶ እስከሚቀልጥም ቢሆን ወዲያውኑ የሚወጣው ፀሐይ ሲያንጸባርቅ፣ ዐይንንም ሆነ መንፈስን ደስ የሚያሰኝ ነው። በተጨማሪም ኮሎራዶ "የአሜሪካው ስዊዘርላንድ" በመባል በሚታወቅባቸውና የ"ሮኪስ ማውንቴንስ" በተባሉ ተራራዎች የተዋበ ስለሆነ ቱሪስቶች በየክረምቱ የሚጎበኙት ስፍራ ነው። ካመት እስከመት በበረዶ ተሸፍነው ከሆስፒታሉ በስተሰሜን የሚታዩት እነዚያ ተራራዎች ደስ ያሰኛሉ።

ወደ ጥበቡ የጤንነት ጉዳይ ስንመለስ፣ ከቶሮንቶው ዶክዩመንት ሌላ የራሳቸውን ምርመራ ሲያካሂዱ ካናዳ ውስጥ ለቀዶ ጥገና የዳረገውን "እየር" ምክንያቱ ምን እንደሆን ለመጀመሪያ ጊዜ አሜሪካኖቹ ደረሱበት። ለካንስ በቆሽቱ መጎዳት ምክንያት የተጠራቀመውን ፈሳሽ ከሆድ ዕቃው ለማውጣት ካናዳዎቹ ባደረጉት ፕሮሲጀር አልፈው ትልቁን አንጀት ሸንቁረውት ኖሯል! እንግዲህ በዚህ ምክንያት ነበር ጥበቡ በአንድ በኩል፡- አምስት ዓመት ከ12 ቀናት በፊጀ ተደጋጋሚ ሕክምና

ነክ ጣጣዎች ውስጥ የገባው። በሌላ በኩልም፡- ቤተሰባችንና የእግዚአብሔር ሕዝብ የእምነትና የተስፋ ተጋድሎ ሲጋደል የከረመው። አሜሪካ መምጣታችንና ዋናው ችግር መታወቁ ግን "ገና ለክብር ይፈለጋል" የሚለውን መልእክት በእምነትና በተስፋ አተኩረን ለመጠበቅ መጋረጃችንን የቀደደ አጋጣሚ ነበር።

*የእፎይታ ጊዜ!*

የዴንቨሩን ከቶሮንቶ ልዩ የሚያደርገው አንዱ ልጆቻችንና ሰፊ ቤተሰቦቻችን በከተማው በመኖራቸው እንደ ካናዳው በርቀት ሳይሆን በየዕለቱ አብሮ መሆን የመቻላችን ጉዳይ ነበር። አሜሪካ ውስጥ በተለያዩ ከተማዎች ያሉም ዘመዶቻችን በቀላሉ እየመጡ ሊያዩን መቻላቸውም ከሩቅ ይጨነቁ ለነበሩ ሁሉ እፎይታ ሆነ። ሌላውና ትልቁ ልዩነት ግን፣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በጥበቡ ላይ መታየት የጀመረው የጤና መሻሻል ነው።

በአንድ ወር ከአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ እቤት ድረስ በሚመጡ ነርሶች አገልግሎት ሊሰጠው የቀረውን የሐኪም ክትትል በውጪ ሊቀጥል ከሆስፒታል ወጣን። የውዴ የጥበቡ እግሮች እንደገና በሕያዋን ምድር በቅዱሳንም ጉባኤ 'መካከል ጌታን ከፍ ከፍ ለማድረግ መመላለስ ጀመሩ። በጸሎትና በምልጃ ከጎናችን ያልተለዩን የዴንቨር የኢትዮጵያ ወንጌላውያን ቤተክርስቲያን ምዕመናን፣ እንዲሁም ፓስተር እንደሻውና ፓስተር ኤርምያስ በሕይወታችን ያላቸው ድርሻ  እንደ ቶሮንቶ ወገኖች እጅግ ታላቅ ነው። አምላካችን የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ያደረገልንን ሁሉ አሜሪካ ውስጥ በጉባኤ ፊት ቆመን የመጀመሪያውን ምስክርነት ለጌታ ክብር የሰጠነው ዴንቨር ኮሎራዶ ነው።

ዴንቨር ሳለን፣ ከእነዚህ በአንዱ ቀን ስልክ ከጥበቡ ዋና መሥሪያ ቤት ከኒውዮርክ ተደወለ።

> *"ጥበቡ ጤናህን በሚመለከት ሁላችንም ከነበረብን ስጋት ስለወጣህ በጣም ደስ ብሎናል፤ እኛ አሁንም ቢሆን የምናስበው ስላንተ ጤንነት እንጂ ስለሥራው አይደለም። ስለሆነም ውጥረትና ውዝግብ ወዳለበት ወደ እስራኤል መልሰን ልንልክህ አንፈልግም። የጡረታ ጊዜህ እስኪደርስ ወደ ዋናው መሥሪያ ቤታችን ልናዞርህ አስበናል። የጤናህንም ጉዳይ በሚመለከት እዚህ አሜሪካ ባሉት እስካሁን በረዱህ ሐኪሞች ክትትሉን ብትቀጥል የሚሻል ይመስለናል። ምርጫህን አስታውቀን!"*

እዎ! "ገና ለክብር ይፈለጋል"። እናም ወደኒውዮርክ በሲንየር አማካሪነት ተቀየርን። ድንቅ ነው እግዚአብሔር እንደተናገረው እንዲሁ ሲሆን ማየት!

****



ምስክርነት በእስራኤል

ኦገስት 2008። ጓዛችንን ከእስራኤል ወደ አሜሪካ ለማንሳት ከጥበቡ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ሄድን። እጅግ ከምንወዳቸውና ከሚወዱን ወገኖቻችን ጋር በሕይወት ያገናኘንን እግዚአብሔር አመሰገንነው። እስራኤል ያሳለፍናቸው የማይረሱ አራት ዓመታት በብዙ ትዝታዎች የታመቁ ናቸው።

በሥራ ተመድቦ እዚያች ምድር ለመኖር እድሉ ይገጥመናል ብለን አላሰብንም። አልመቻች ብሎን ነው እንጂ ለጥቂት ቀናት ጎብኝቶ ለመመለስ ግን ተመኝተናል። እንዲያውም ከቅርብ ጓደኞቻችን ጋር ለአንድ ፋሲካ በዓል ካቀድን ወዲያ እነሱ ሳይመቻቸው ቀረና ለሌላ ጊዜ አስተላለፍነው። ኋላ ግን እነዚያ ጓደኞቻችንን እስራኤል ቤታችን 10 ቀናት እንግዶቻችን ሆነው ምድሪቷን እንድናስጎበኛቸው አድርጓል እግዚአብሔር።

እስራኤል የሚገኙ ቁጥራቸው ጥቂት የማይባል ቤተ-እስረኤላውያን ከኢትዮጵያ ወደ ተስፋይቱ ምድር ተሻግረዋል፤ እግዚአብሔር አምላክ በጥንት ነብያት አፍ "እስራኤልን የበተነ እርሱ ይሰበስበዋል" ብሎ በተናገረው መሠረት። በእርግጥም ከምድር ዙሪያ ሁሉ ሕዝበ እስራኤልን እየሰበሰበ ባለበት ዘመን ውስጥ እንዳለን እኔና ጥበቡም በአካል በዚያች አስደናቂ ምድር ኖረን የዐይን ምስክሮች ሆነናል። እኛም ከካሌብና ከኢያሱ ጋር ተደምረን ስለተስፋይቱ ምድር ያየነው፣ ከዐለት ድንጋይ ውስጥ ውሃን የሚያመነጨው የእስራኤል አምላክ እንደተናገረ ማርና ወተት የምታፈስ የተባረከች ምድር መሆኗን ነው።

በሄድንባቸው አገሮች ሁሉ በወገኖች ሕብረት የባረከን እግዚአብሔር በእስራኤል ምድርም ይህንኑ ደግሞ አሳይቶናል። እግዚአብሔር "ሕዝቤ" ባለው ሕዝብ መካከል ተገኝተን በፍቅራቸው ተገልግለናል። ጌታ ክርስቶስን እንደግል አዳኛቸው አድርገው የተቀበሉ፣ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው በልሳን የሚናገሩ፣ ቤተእስራኤላውያን ወገኖቻችንን ስናገኝ ደስታችን ወሰን አልነበረውም።

ምንጊዜም የማንረሳቸውን ሕብረትና አንድነት ከእነዚህ ወገኖቻችን ጋራ ተካፍለናል። በእነዚያ ጥቂት ዓመታት እንደ ልጆቻችን እንደ እህት ወንድሞቻችን በሆኑልን ወገኖች መሐል ማገልገልም ሆነ መገልገል ብዙ በረከትን አትርፎልናል። ዳዲ እንደዚያ ባለ በሞትና በሕይወት መሐል በነበረበትና በምድር ዙሪያ በጥብቅ ይጸለይ በነበረበት ጊዜ፣ እስራኤል አንዱና ትልቁ የጸሎት ተጋድሎ የተደረገበት ስፍራ ነበር። እነዚያን የሞት ጥላዎች ሁሉ ከዳዲ ላይ አንስቶና እንደገና በሕያዋን ምድር እሱን በመካከላቸው ሲያቆመው የእህት የወንድሞቻችን ደስታና መጽናናት ብዙ ነበር። ለጥቂት ቀናትም ቢሆን የምስጋናና የምስክርነት ጊዜ በእስራኤል ምድር እግዚአብሔር አምላክ ሰጠን። እስራኤል በጌታ ካፈራናቸው እነዚህን ከመሳሰሉ ወገኖቻችን መለያየቱ ከባድ ቢሆንም፣ ሁላችንም "የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን!" ማለትን መረጥን።



ምስክርነት በኢትዮጵያ

የጥበቡ መሥሪያ ቤት ባልደረቦቹም ያን ከመሰለ አስጊ ሁኔታ ወጥቶ በመካከላቸው ሲያዩት ደስታቸው ከፍ ያለ ሆነ። በጣም ስለሚወዱት መሄዱን ባይፈልጉትም ከሞት ተርፎ ወደ ኒውዮርክ ለመዛወር መብቃቱ እጅግ አስደነቃቸው። እናም የምስጋናና የሽልማት ስጦታዎች አበርክተውለት በትልቅ ክብር ሸኙት! "ኒውዮርክ ለክብር ስለሚፈለግ!"

ከእስራኤል ጉዟችንን ወደ ኒውዮርክ ከመቀጠላችን በፊት ከውዱ ከጥበቡ ጋራ ወደ አገራችን ኢትዮጵያም ጎራ አልን። አስበነው አይደለም፤ ለካስ ምድራችን የገባነው ከናዳ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በጤና በታመመበት ቀን፣ በኦገስት 19 ኖሯል! ልክ ከአንድ ዓመት በኋላ!

ይህን ያስተዋሉ ጓደኞቻችን፡- "ጠላታችን ባስለቀሰን ቀን ፈንታ አምላካችን የደስታና የእንባ መታበሻ ቀን አደረገልን" በማለት እግዚአብሔርን አመሰገኑ። ዳግም በምድር ላይ ቆመው ይመላለሳሉ ብሎ በአእምሮ ቢታሰብ አስቸጋሪ የነበሩት፣ እግዚአብሔርን ታምነን ግን የተነበይንባቸው የጥበቡ እግሮች፣ የፈጣሪያቸውን ሁሉን ቻይነት ሊመሰክሩ በታላላቅ ጉባኤ መሐል በድል ሲመላለሱ አየን። እናም እግዚአብሔር "ገና ለክብር ይፈለጋል" ሲል የገዛ ከንዱን ተማምኖ በተናገረው መሠረት በመንግሥታቱ ዋና መሥሪያ ቤት ለሌላ ክብር ወሰደን።

የጡረታ ዕድሜው ከመድረሱ በፊት የቀረውን መጨረሻ አንድ ዓመት የዓለም ዋና ከተማ ተብላ በምትታወቀው ኒውዮርክ! እኔና ውዴ ባማረና የከተማይቱን ውበት ከቤታችን በጉልህ ማየት በምንችልበት ውብ መኖሪያ ቤት አሳለፍን። በብዙ የዩኤን ሰራተኞች በሚፈለግ ቦታ "ሩዝቬልት አይላንድ" ተብሎ በሚታወቀው ደሴት ላይ እኔንና ጥበቡን አምላካችን አስቀመጠን! ለመሥሪያ ቤቱም ቅርብና አመቺ ቦታ ነው። ለኛ የዕረፍትና በዘመናችን ሁሉ ስለሰሙ ሲል በላያችን ስለተገለጠው የእግዚአብሔርን ምሕረትና ቸርነት የምናጣጥምበት ጊዜ ሆነልን። አዎን! በዚያች በውሃ በተከበበች ደሴት እኔንና ጥበቡን አስቀምጦ፣ በዘመናችን መጨረሻ ላይ አምላካችንን የምናመሰግንበት ወቅት... ፈረንጆች እንደሚሉት፣ በዐይነቱ ልዩ የሆነ "የሃኒ ሙን" ጊዜ አደረገልን።

የጤናውን ሁኔታ በሚመለከት ደግሞ ዴንቨር ኮሎራዶ የያዘውን ሪከርድ በሙሉ ለኒውዮርክ አቀበለ። "ኒውዮርክ ፕሬስቢቴርያን" በተሰኘው ስመጥር ሆስፒታል በቆሸትና በሆድዕቃ ሕክምና በታወቁ እስፔሺያሊስቶች ክትትሉን ቀጠልን። ኒውዮርክ ባሳለፍነው በዓመቱ መካከል ሆስፒታል መግባት ባስፈለገው ጊዜ ሁሉ የተራቀቀ አገልግሎታቸው ተጠቃሚ ሆኗል። ዴንቨርም ሆነ ኒውዮርክ ያጋጠሙን ሐኪሞች ባብዛኛው እጅግ መልካም ሰዎች ነበሩ። አምላኩ እግዚአብሔር በላዩ ካስቀመጠው ሞገስ የተነሳ ስለሚያደርጉለት ሕክምና በቅድሚያ አማክረውትና ተግባብተው ነው። እንደ አንድ የሥራ ጓደኛቸው ሃሳቡን ያደምጣሉ፤ አስተያየቱን ይቀበላሉ፤ የአእምሮውን ብሩህነት ያደንቃሉ። ለጥበቡ ያላቸው ፍቅር አክብሮትና ርህራሄ ሁሌም ሳስበው ይገርመኛል። ከእነዚህ ሐኪሞች መሐል የማልረሳት አንዷ እንዲህ ብላ ነበር፡-

> "በሥራው የታወቀ በጣም የምወደው ሐኪም አባት አለኝ። አንተ አባቴን ትመስለኛለህ፤ በትዕግሥትህና በገጽታህ ላይ ሁሌ በማየው ሰፊ ፈገግታ። እኔ ደግሞ ሰውን አባቴን ትመስለኛለህ እንዲህ በቀላሉ ብዬ አላውቅምና ምን ያህል እንደማከብርህ በዚህ መገመት ትችላለህ!"

መሥሪያ ቤቱ ለጥበቡ ያደረገውን አስገራሚ እንክብካቤ አሁን ላይ ሆኜ ሳስበው እደነቃለሁ። ሌሎችም የሥራ ባልደረቦቹ ስለተደረገለት ክብርና እንክብካቤ ይደነቃሉ። ኒውዮርክ ከተዛወርን በኋላ እንኳ፣ እንደርስው ለህያ ዓመታት መሥሪያ ቤቱን ያገለገለውን አንድ ሰው ቀጣይ ሥራ የለንም ብለው ሲያሰናብቱት ጥበቡ ግን፣

"የሚያሳስበን የጤናህ ጉዳይ እንጂ የሥራህ አይደለምና ስትችል ብቻ ግማሽ ቀን እየገባህና እያረፍክ ሕክምናህን ተከታተል"

ተብሏል! በስሙ ላይ ተጓደንና ተመክተን በዘመናችን ሁሉ ለሰበክነውና ለመሰከርነው እውነት ጠላታችን በበቀልና በብስጭት የተነሳ ቢሆንም እግዚአብሔር አባታችን ደግሞ፡- "ልጄን ማስታመም ካስፈለገም እንዲህ መኝታውን አነጥፍለታለሁ" ሲል በዲያብሎስ ላይ ወጥቷል። የእግዚአብሔር ቃል በመዝሙር 41፥1-3 እንደሚለው ማለት ነው።

"ለችግረኛና ለምስኪን የሚያስብ ምስጉን ነው፤ እግዚአብሔር በክፉ ቀን ያድነዋል፤ እግዚአብሔር ይጠብቀዋል፣ ሕያውም ያደርገዋል፣ በምድር ላይም ያስመሰግነዋል፣ በጠላቶቹም ፊት አያሳልፈውም። እግዚአብሔር በደዌው አልጋ ሳለ ይረዳዋል፤ መኝታውን ሁሉ በበሽታው ጊዜ ያነጥፍለታል።"



ኒውዮርክ ዲሴምበር 2008

ጥበቡ ኃይለሥላሴ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል ጉስቁልና፣ ጦርነት፣ ረሃብና ድህነት የተጫነውን፣ የተለያየ ምስኪን ሕዝብ፣ በቅንነትና በትጋት ያገለገለበትን፣ አምላካችን የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር አየ። ለዚህ ታማኝ ባሪያው ከአእምሮ በላይ የሆነ እንክብካቤን ያደርግለት ዘንድ የዐለም መንግሥታቱን ድርጅት አስነሳው።

****

*ሴፕቴምበር 30/2009።* የጡረታ ዕድሜው ስለደረሰ ሙሉ መብቱ ተከብሮለት የኒውዮርክ ቆይታችንን ከልዩ ምስጋናና መልካም አሸኛኘት ጋር ተጠናቀቀ። ሰይጣን እንደተመኘው ሳይሆን በዩኒሴፍ ላለፉት ሀያ ዓመታት ጥበቡ ኃይለሥላሴ በቅንነትና በትጋት ያበረከተውን አገልግሎት እግዚአብሔር በክብር ቋጨልን። ወደ አገራችን ኢትዮጵያ ደግሞ ገብተን እንደ አንድ ዜጋ የሚጠበቅብንን ለማበርከት ጓዛችንን ይዘን ተነሳን፤ ኦክቶበር 25/ 2009።



ዴንቨር ሴፕቴምበር 2010

****

*የድል ምስክርነት በቶሮንቶና ዲትሮይት!*

ኖቬምበር 2010። "ይሄን ሕንጻ እንኳን ላርፍበት ባጠገቡ ባለፍኩ ቁጥር ገላምጬው፣ ተቆጥቼው ነው የማልፈው!"

የፓስተር ዘካርያስ ንግግር ነው። ይህን ያለው የድል ምስክርነታችንን ለእግዚብሔር ክብር በቅዱሳን መሐል ለመስጠት ቶሮንቶ በገባን ዕለት ነበር። ካናዳ ያሳለፍናቸው እነዚያ አስጨናቂ ስድስት ወራት ትዝ እያሉት ነው ፓስተር፤ ያረፍነው ደግሞ እዚያው ማውንት ሳይናይ ሆስፒታል አጠገብ ካለው ሆቴል ከኖርኩበት መሆኑ ገርሞት ነው። የጥበቡን ቀብር ቶሮንቶ ሊያደርግ የተመኘው ጠላታችንን ከፍታ ያስረገጠን አምላካችን ይክበር! ኢየሱስ የጌቶች ጌታ ነው!

"... ጠላቶችህም ይገዙልሃል አንተም ከፍታቸውን ትረግጣለህ" ዘዳ 33፥29። ታላቅ የመጽናናትና የድል ጊዜ በቶሮንቶ ካናዳና እንዲሁም በዲትሮይት ሚቺጋን አደረገልን እግዚአብሔር! እነዚያ በድን የነበሩት የጥበቡ እግሮች እግዚአብሔርን ሊያመልኩ ሊሰግዱና የአምላኩን ታላቅነት ሊናገሩ በተለያዩ ስፍራዎች ቆመዋል። የቶሮንቶው ግን የምስክርነቶቻችን ሁሉ ቁንጮ ነው!

****



የድል ምስክርነት በቶሮንቶ!



ምስክርነት በዲትሮይት



ዲትሮይት ሚቺጋን

# አስጨመረልን ሞገስ አስደረበልን ካባ!

*ይህን የጻፍኩት ጃንዋሪ 2008 (እ.ኤ.አ) ነው። ከቶሮንቶው ማውንት ሳይናይ ሆስፒታል ወደ አሜሪካ በልዩ አውሮፕላንና ከብር ለተጨማሪ ሕክምና እንድንወስድ ጌታ ሲያደርግ፣ ቀብሩን በክናዳ ሊፈጸም ከታገለን ከሞት ጉያ ባለቤቴን ስላወጣልኝ የጻፍኩት ነው። ለመጀመሪያ ጊዜም ያነበብኩት የቶሮንቶን ቅዱሳን ስንሰናበት ነበር፣*

እግዚአብሔር አምላክ በአዳምና ሔዋን ውድቀት ምክንያት በኃጢአት ቀንበር ውስጥ ለወደቀው የሰው ልጅ እንዲህ አለ።

የኔ ወዳጅ እንዳትሆን ዘርክን ከኔ የነጠለው
ኃጢአተኛ በደለኛ ልበ ደንዳናና አመጸኛ፤ መሆንህ እውነት ነው

ሆኖም ግን፦

ከዚህ ሁሉ ነፃ የምትወጣበት.....እንደገናም የኔ የምትሆንበት
መንገዱ አንድና አንድ ብቻ ነው......እርሱም ይቅርታዬ ነው
በምወደው ልጄ የምገልጠው ምሕረቴ ነው።
አዎን! ሰው ሆይ! ከዘላለም ሞት የምትተርፈው
እውነት የሆነው ኃጢአትህ......ጥልቅ በሆነው ምሕረቴ ሲደመሰስ ብቻ ነው።
አለና፦ ኃጢአት ሊያስከትል የተገባውን ዘላለማዊ ሞት......የነፍሳችን ለውጥ የሱስ ጌታ ሽሮት
አብ በልጁ ያስገኘልን እውነትና ምሕረት.........አስወጥቶናል እርንት!

ታዲያ፦ይሄን የማይወድ የሰው ዘር ጠላት......ሲነድ ይኖራል በራስ ምታት

ስለዚህ፦ ስለዚህ፦ይህ ባላጋራችን
ይዞራል.. ያደባል... ያሰላል... ያጠምዳል
ቢሆንለት.. ቢሳካለት... አንድ ቀን ብንገኝለት.....ይሞክራል ሳይታክት

ለምን? ቢባል.......እግዚአብሔር አምላክ፦
በመካከልህ አድር ዘንድ መቅደስን ሥራልኝ ያለውን፤ ሕዝቡና ርስቱ ያረገውን
ከኃጢአት ካበሳው በልጁ ደም ያጠበውን...ሰው...... ለመጣል፦
ሳይሆን ቢቀር ለማድከም..... ሁሌ ይጥራል
ለምሳሌ፦

ባለፈው ሁለት ሺህ ሰባት.....ዲያብሎስ ሙከራው ቢሰምርለት
እንደ ጥረቱ ቢሆን ኖሮ... ቢሳካለት
ለቤታችን የደገሰው የሃዘን ጽዋ ምሬት፤ ......ሚያንገደግድ ነበር ከቆምንበት

ኢየሱስ፦ "የጌቶች ሁሉ ጌታ ነው" ባልንበት፤ ፈዋሽነቱን ድንቅ አድራጊነቱን ባወጅንበት
ሞትና ሲዖልን ድል መንሳቱ...... በትንሳኤው ጉልበት፤ ዓለታችን የጸናንበት.....አምላካችን የታመንበት
በማንነቱ በመመካት......በዘመናት መሃል የተጓደድንበት፤
"ኢየሱስ ያድናል! ኢየሱስ ያዋጣል! ኢየሱስ ከሞትም ይታደጋል!" ያልንበት፤
ሊታይ ሊፈተን በከፋት የጨለማ ኃይላት፤ ምክክሩ ተጧጧፈ .....ለሞት ....ወይ ለሽረት!
በመጀመሪያ... በመጀመሪያ.... አሉ ስይጣናት ሲማከሩ...
ይጠበቅልን ሚስጥሩ.....እንዳይከሽፍብን ሃሳባችን ገና ከጅምሩ

እስቲ ረቂቅ በምትባለው፤ በመካከለኛ ልጃቸው
የሞት ወጥመዳችንን እንዘርጋው.....ይታያል ያኔ ያ ግትር እምነታቸው

አጥፊ መሳሪያችንን.....እንዘርጋ አውታራችንን

አምላክህ እግዚአብሔር አለውና መልሰ
ጨካኝ ሃሳቡን የሞት ድግሱን፤ አንገድጋጅ ጽዋ የሚመረውን
በጽልመት ጎዳው ያዘጋጀውን፤ በዝርዝር ያየ ጌታ እግዚአብሔር
እኛን ሊያስመልጥ ወጥመድ ሊሰብር፤ ለማዳን ወጣ ሞትን ለመሻር!
ሆነ ትርምስ ባጋንንት መንደር፤ ወዴት ይድረሰው አትውጠው ምድር
ያሰበው ሁሉ ናላው እስኪዞር፤ መና ቀረና ሰንቱ ምክክር
በጸጸትና በፍርሃት... እየሰገደ በውርደት፤ እንዲህ ሲል ተናዘዘ የማይክደውን እውነት

"አይ የኔ ነገር! ዛሬም ደግሜ መርሳቴ!! የማይነካ መንካቴ ጠር ሆኖ ይኖራል ለመንግሥቴ!
እግዜር በጸጋው ያዳነውን.... .እርስቴ ብሎ የለየውን በደሙ አንጽቶ ያጠበውን......እንዳይኑ ብሌን የሚያየውን
ያን ሕዝብ የሚነካ....የዓይኑን ብሌን እንደሚነካ፤ በዚያ ቃል በማይሻረው ተጽፎ ኖሯል ለካ!
ለካስ ለካ....ባምላኩ መንፈስ የተነካ፤ አይነካም ለካ!!

እጥፍ ይቅርታ ላረግሁት ጥፋት፤ መጥቼ ጉድ ሆንኩ ባድራሻ ስህተት
ቢል ቢቀባጥር ቢሞላ ጸጸት፤ ማን ሊሰማው ነው የውሸት አባት
በእጥፍ በድርብ ሊቀጣው ቅጣት፤ ጌታ መጣበት በበቀል እሳት
ጠላቴ ሆይ! ስማ! ዛሬም እነግርሃለሁ!
የማይዋጥልህን እውነት አስታውቅሃለሁ
አንተው በጫርከው ባሴርከው ደባ
አስጨመርከልን ሞገስ አስደረብከልን ካባ !!
እግዚአብሔርን ለሚወዱ እንዳሳቡም ለተጠሩ፤ ለበጎ እንዲሆን ነገር ሁሉ
ዛሬም መርሳትህ ይገርመኛል ይደንቀኛል፤ ለኔ ግን ተመችቶኛል!

ምክንያቱም!
አንተ ከጥልቅ ከፋትህ......አውጥተህ አውርደህ
አሁን ነው እድሌ ያልከበት ........እርስዋን የማገኝበት
ነገር ሁሉ ተለውጦ........ሲሆን አውቃለሁ ተገልብጦ፤ ያምላኬ ክብሩ ተገልጦ
ክብርና ምስጋና ለጌቶቹ ጌታ፤ ለሠራዊት አምላክ ጠላቴን ለረታ
ያዘን ማቄን ጥሎ ለሞላኝ እልልታ
ከጥግ እስከጥግ በምድር ዙርያ፤ ስለኛ የቆማችሁ በንጉሱ ማደሪያ
ምርኮው ተመልሷል ከዲያብሎስ ጉያ፤ ክብር ላምላካችን እንበል ሃሌ ሉያ!!

****